# የሰባቱ አብያተክርስቲያናት ዘመን

## ምእራፍ አንድ

## የኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ

**ራዕይ 1፡1 - 20**

*ቶሎ ይሆን ዘንድ የሚገባዉን ነገር ለባሪያዎቹ ያሳይ ዘንድ እግዚአብሔርለኢየሱስ ክርስቶስ የሰጠዉ በእርሱም የተገለጠዉ ይህ ነዉ፡ኢየሱስም በመልአኩ ልኮ ለባርያዉ ለዩሐንስ አመለከተ*

*እርሱም ለእግዚአብሔር ቃል እና ለኢየሱስ ክርስቶስ ምስክር ላየዉምሁሉ መሰከረ፡፡*

*ዘመኑ ቀርቦአልና የሚያነበዉ የትንቢቱን ቃል የሚሰሙትና በዉስጡ የተጻፈዉንየሚጠብቁት ብጹዓን ናቸዉ፡፡*

*ዮሐንስ በእስያ ላሉት ለሰባቱ አብያተክርስቲያናት ካለዉና ከነበረዉከሚመጣዉም በዙፋኑም ፊት ካሉት*

*ከሰባቱ መናፍስት ከታመነዉም ምስክር ከሙታንም በኩር የምድርም ነገስታት ገዥ ከሆነ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን ለወደደን ከሃጢያታችንምበደሙ ላጠበን*

*መንግስትም ለአምላኩ ና ለአባቱም ካህናት እንድንሆን ላደረገ ለእርሱ ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ክብርና ኃይልይሁን አሜን፡፡*

*እነሆ ከደመና ጋር ይመጣል ዓይንም ሁሉ የወጉትም ያዩታል የምድርም ወገኖች ሁሉ ስለ እርሱ ዋይ ዋይ ይላሉ፡፡ አዎንአሜን፡፡*

*ያለዉና የነበረዉ የሚመጣዉም ሁሉንም የሚገዛ ጌታ አምላክ፡፡ አልፋና ዖሜጋ እኔ ነኝ ይላል፡፡*

*እኔ ወንድማችሁ የሆንሁ ከእናንተም ጋር አብሬ መከራዉንና መንግስቱንየኢየሱስ ክርስቶስንም ትዕግስት የምካፈልዮሐንስስለ ኢየሱስ ምስክር ፍጥሞ በምትባል ደሴት ነበርሁ*

*በጌታ ቀን በመንፈስ ነበርሁ በኋላዬም የመለከትን ድምጽ የሚመስል ታላቅ ድምፅ ሰማሁ*

*እንዲሁም፡፡ የምታየዉን በመጽሐፍ ጽፈህ ወደ ኤፌሶንና ወደ ሰምርኔስ ወደ ጴርጋሞንም ወደ ትያትራንም ወደ ሰምርኔስምወደ ፊላደልፊያም ወደ ሎዶቂያም በእስያ ወዳሉት ወደ ሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት ላክ አለኝ፡፡*

*የሚናገረኝንም ድምጽ ለማየት ዘወር አልሁ ዘወርም ብዬ ሰባት የወርቅመቅረዞች አየሁ*

*በመቅረዞቹም መካከል የሰዉ ልጅ የሚመስለዉን አየሁ እርሱም እስከእግሩ ድረስ ልብስ የለበሰዉ ደረቱንም በወርቅ መታጠቂያ የታጠቀ ነበር፡፡*

*ራሱና የራስ ጸጉሩም እንደ ነጭ የበግ ጠጉር እንደ በረዶም ነጭ ነበሩአይኖቹም እንደእሳት ነበልባል ነበሩ*

*እግሮቹም በእቶን የነጠረ የጋለ ናስ ይመስሉ ነበር ድምፁም እንደብዙዉኃዎች ድምፅ ነበረ፡፡*

*በቀኝ እጁም ሰባት ከዋክብት ነበሩት ከአፉም በሁለት ወገን የተሳለስለታም ሰይፍ ወጣ ፊቱም በኃይል እንደሚበራ እንደጸሐይ ነበረ፡፡*

*ባየሁትም ጊዜ እንደሞተ ሰዉ ሆኜ ከእግሩ በታች ወደቅሁ ቀኝ እጁንምጫነብኝ እንዲህም አለኝ፡፡ አትፍራ ፊተኛዉ እና መጨረሻዉ ሕያዉም እኔ ነኝ*

*ሞቼም ነበርሁ እነሆም ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ሕያዉ ነኝ የሞትናየሲኦልም መከፈቻ አለኝ፡፡*

እንግዲህ ያየኸዉን አሁንም ያለዉን ከዚህም በኋላ ይሆን ዘንድ ያለዉንጻፍ፡፡

*በቀኝ እጄ ያየሃቸዉ የሰባቱ ከዋክብትና የሰባቱ የወርቅ መቅረዞችሚስጢር ይህ ነዉ ሰባቱ ከዋክብት የሰባቱ አብያተክርስቲያናት መላእክት ናቸዉ ሰባቱም መቅረዞች ሰባቱ አብያተክርስቲያናት ናቸዉ፡፡*

### የምእራፍ አንድ መግቢያ

ራዕይ 1፡1-3

*“ቶሎ ይሆን ዘንድ የሚገባዉን ነገርለባሪያዎቹ ያሳይ ዘንድ እግዚአብሔር ለኢየሱስ ክርስቶስ የሰጠዉ በእርሱም የተገለጠዉ ይህ ነዉ፡ኢየሱስም በመልአኩ ልኮ ለባርያዉለዩሐንስ አመለከተ እርሱም ለእግዚአብሔር ቃል እና ለኢየሱስ ክርስቶስ ምስክር ላየዉም ሁሉ መሰከረ፡፡ ዘመኑ ቀርቦአልና የሚያነበዉየትንቢቱን ቃል የሚሰሙትና በዉስጡ የተጻፈዉን የሚጠብቁት ብጹዓን ናቸዉ፡፡”*

የዚህ መጽሃፍ ጸሀፊ ወይም ደራሲ ቅዱስ ዮሃንስ ሳይሆን ደራሲዉ አምላክነዉ የታሪክ አጥኒዎች እንደሚስማሙት ዮሃንስ የመጨረሻዉን ህይወቱን የኖረዉ በኤፌሶን ሲሆን ይሄን መጽሃፍ የጻፈዉም ጲጢሞስ በምትባልደሴት ዉስጥ ነዉ፡፡ ነገር ግን ቁጥር 3 ላይ የትንቢቱን ቃል የሚሰሙት ብሎ እንደሚገልጸዉ ወደፊት በሚመጡት የአብያተክርስቲያናትዘመን የኢየሱስ ክርስቶስን መገለጥ ያሳያል በትክክልም የሆነዉ ይህ ነዉ፡፡

ይህ መጽሃፍ በተለምዶ የዮሃንስ ራእይ ተብሎ ቢሰየምም ስህተት ነዉ ትክክለኛዉመሆን ያለበት በሁሉም የአብያተ ክርስቲያናት ዘመን የኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ ነዉ፡፡ ለዮሃንስ የታየ ወይም የተሰጠ መገለጥ ነዉ፡፡

በመጽሃፍ ቅዱስ ዉስጥ የመጨረሻዉ መጽሃፍ ነዉ ነገር ግን የወንጌልን ጅማሬእና መደምደሚያ የሚነግረን መጽሃፍ ነዉ፡፡

በግሪክ መገለጥ የሚለዉ ቃል አፖካሊፕስ ሲሆን ይህም ማለት ገለጠ ማለትነዉ፡፡ ይህ መገለጥ አንድ የቅርጻ ቅርጽ ባለሙያተኛ የሀዉልት ስራዎቹን ለተመልካቾቹ እንደሚገልጥበት ምሳሌ በደንብ ተገልጿል በፊትተከድኖ የነበረዉን መግለጥ ማለት ነዉ፡፡ የተከፈተዉም የኢየሱስ ክርስቶስ በአካል መገለጥ ብቻ ሳይሆን በሚመጡት ሰባቱ አብያተክርስቲያናትምዘመን የሚገለጥበትን መገለጥ ጭምር ነዉ፡፡

በመንፈስ ቅዱስ የሚገኝ መገለጥ ለእዉነተኛ አማኝ የሚሰጠዉ ጥቅም ፈጽሞ የማይጋነን ነዉ እናንተ ከምታስቡት በላይ መገለጥ እጅግ አስፈላጊ ነዉ፡፡እያወራሁ ያለሁት መገለጥ ለሁሉም አይነት መገለጥ ነዉ ለቤተክርስቲያን እጅግ በጣም አስፈላጊ ነዉ፡፡

ታስታዉሳላችሁ በማቴዎስ 16 ላይ ጌታ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቶቹን እንዲህብሎ ሲጠይቃቸዉ “ሰዎች የሰዉን ልጅ ማን ይሉታል” እነርሱም እንዲህ አሉት አንዳንዶችመጥምቁ ዩሃንስ ነዉ ይላሉ፤ አንዳንዶች ኤልያስ ይላሉ ሌሎች ደግሞ ኤርምያስ ወይም ከነብያት አንዱ ነዉ ይላሉ፡፡ እርሱም መልሶእንዲህ አላቸዉ እናንተስ ማን ትሉኛላችሁ እናም ስምኦን ጴጥሮስ እንዲህ ብሎ መለሰ አንተ የተቀባህ የህያዉ የእግዚአብሔር ልጅ ነህኢየሱስም መልሶ የዮና ልጅ ስምኦን ሆይ የተባረክህ ነህ እነሆ ስጋ እና ደም ይህን አልገለጠልህም በሰማይ ያለዉ አባቴ ገልጦልሃልና እነሆ እላችኋለሁ ጴጥሮስ ሆይ በዚህ አለት ላይ ቤተክርስቲያኔን እገነባለሁየገሀነም ደጆችም ሊቋቋማት አይችሉም፡፡ የሮም ካቶሊክ ቤተክርስቲያን የተመሰረተችዉ በጴጥሮስ ላይ ነዉ ይላሉ ይሄ ከስጋነዉ ምክንያቱም በምን አይነት መንገድ ነዉ እግዚአብሔር ባልተረጋጋ እና ኢየሱስን በካደዉ ሠዉ ላይ ቤተክርስቲያኑን የሚገነባዉ እግዚአብሔርከሐጥያት በተወለደ በማንም ሰዉ ላይ ቤተክርስቲያኑን ሊገነባ አይችልም፡፡ የሆነ ቦታ ላይም እግዚአብሔር ቀድሶ ባቀመጠዉ አለት ላይምአይደለም የተገነባችዉ በመገለጥ ላይ ነዉ፡፡ እስኪ እንደተጻፈዉ መንገድ አንብቡት “ስጋና ደም አልገለጠልህም ነገርግን በሰማይ ያለዉ አባቴ ገለጠልህ እንጂ እናም በዚህ አለት(መገለጥ) ላይ ቤተክርስቲያኔን እገነባለሁ ፡፡ቤተክርስቲያን የተገነባችዉ በመገለጥ ላይ ነዉ”እነሆ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል “

አቤል ለእግዚአብሔር ደስ የሚያሰኘዉን መስዋእት ማቅረብ እንዴት አወቀ?በእምነት ለመስዋእትነት ደም ማቅረብ እንዳለበት መገለጥን ተቀበለ፡፡ቃየን ግን ይሄን መገለጥ አላገኘም (ምንምታዛዥ ቢሆንም እንኳን)ስለሆነም ተገቢ የሆነዉን መስዋእት ማቅረብ አልቻለም፡፡ ልዩነትን ያመጣዉና አቤልን የዘላለም ህይወት የሰጠዉ ከእግዚአብሔር ያገኘዉመገለጥ ነዉ፡፡ የሚያነጻችሁ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም እንደሆነና የሚያድናችሁ እግዚአብሔር እንደሆነ እግዚአብሔር እስኪገልጥላችሁድረስ መጋቢዎች የሚነግሯችሁ ወይም በየሴሚናሩ የሚያስተምሩት የሚያኮራ ሊመስላችሁ ይችላል፡፡ ወደ ዘላለማዊ ህይወት የሚያስገባችሁመንገድ መገለጥ ብቻ ነዉ፡፡

ቀደም ሲል እንዳልኳችሁ ይህ የራእይ መጽሀፍ የኢየሱስ ክርስቶስን መገለጥእና በሰባቱ የአብያተ ክርስቲያናት ዘመን የሚሰራቸዉን ተግባራት የሚገልጽ መጽሃፍ ነዉ፡፡ ይህ መገለጥ ነዉ ምክንያቱም ደቀመዛሙርቶቹእንኳን ይሄን የተጻፈዉን እዉነት አላወቁትም ነበርና ታስታዉሳላችሁ በሐዋርያት ስራ መጽሃፍ ላይ ወደ ኢየሱስ መጥተዉ ይሄን ጥያቄጠየቁት ''ጌታ ሆይ በዚህ ወራት ለእስራኤል መንግስትን ትመልሳለህን?'' እናም እንዲህ አላቸዉ “አብ በገዛ ስልጣኑ ያደረገዉንወራትና ዘመናት ታዉቁ ዘንድ ለእናንተ አልተሰጠም” ደቀ መዛሙርቱ አሁንም ድረስ ኢየሱስ በምድር ላይ ያለ መንግስት እንደሚኖረዉእንደሚመሰረት ያስቡ ነበር፡፡ ነገር ግን እርሱ ሊገነባ ያለዉ መንፈሳዊ መንግስት ነበር በሚመሰርተዉ መንግስት የእርሱ ቦታ ምንእንደሆነ እንኳን አልነገራቸዉም አብ ለእርሱ አልገለጠለትም ነበርና ነገር ግን ሞትን ድል አድርጎ ከተነሳ በኃላ በዚህ ጊዜ በማስታረቅአገልግሎቱ ላይ በቀጥታ ለዮሃንስ በመገለጥ ነበር የእሱን ክብር እና ከቤተክርስቲያን መገኘት ትርጉምና ተግባሩን ለመግለጥ የቻለዉ፡፡

በዚህ መገለጥ የሰይጣንን መጨረሻ ይነግረናል፡፡ ከዲያብሎስ ጋር እንዴትእንደሚጋፈጠዉ እና ወደ እሳት ባህር እንደሚጥለዉ ይነግረናል፡፡ ሰይጣንን የተከተሉ ሁሉ መጨረሻቸዉ ምን እንደሆነ ይገልጥልናል ይሄንመገለጥ ደግሞ ሰይጣን ይጠላዋል፡፡

ከመጽሐፍ ቅዱስ መጻህፍቶች ዉስጥ ከሌሎቹ ይበልጥ ሁለት የሚጠላቸዉመጻህፍቶች እነማን እንደሆኑ ታስተዉላላችሁ? በስነ-መለኮት ሊቃዉንት እና በሀሰተኛ የሣይንስ ምሁራን በኩል የኦሪት ዘ ፍጥረት መጽሃፍንእና የራእይ መጻህፍን ሁለቱን መጻህፍት ሁልጊዜ ለማጥቃት ይሞክራል፡፡ ምክንያቱም በእነዚህ መጻህፍት ዉስጥ የሴይጣንን መነሻ ከፉመንገዶች እና የመጥፊያ መንገዱን የምናገኝባቸዉ መጻህፍቶች ናቸዉ፡፡ ለዛ ነዉ ሁል ጊዜ የሚያጠቃቸዉ፡፡ መጋለጥን ይጠላዋልና፡፡በእነዚህ መጻህፍት ደግሞ ማንነቱ በትክክል የተገለጠ ነዉ፡፡ ኢየሱስ ስለ ሴይጣን እንዲህ አለ ከእኔ ጋር አንዳች ክፍል የለዉምእኔም አንዳች ህብረት የለኝም ዲያብሎስ ልዩነቱን ለማረጋገጥ ይፈልጋል ነገር ግን አልቻለም፡፡ ስለሆነም በቃሉ ላይ ሰዎች መተማመንእንዳይኖራቸዉ ለማድረግ የቻለዉን ሁሉ ይሞክራል፡፡ ነገር ግን ቤተክርስቲያን ሰይጣንን ማመን ስትተዉ እና የቃሉን በመንፈስቅዱስመገለጥ ስታምን ያን ጊዜ የገሀነም ደጆች አይቋቋሟትም፡፡

ቅር የማይላችሁ ከሆነ እስኪ ከእራሴ የአገልግሎት ህይወት ልንገራችሁ በህይወቴ እየተገለጡ ያሉት ስጦታዎችከተፈጥሮ በላይ እንደሆኑ ሁላችሁም ታዉቃላችሁ በሰዎች ልብ የተሰወረን ሃሳብ እና የበሽታን አይነት መለየት እንዲሁም ሌሎችእግዚአብሔር ብቻ ሊያዉቃቸዉ የሚችሉነገሮችን ለእኔ የሚገለጥልኝ ከመንፈስቅዱስ የሚገኝ ስጦታ ብቻ ነዉ፡፡ ሰይጣን ሊጋለጥእንደሆነ ሲያዉቅ የሠዎች ፊት ላይ የሚነበበዉን ነገር ከአጠገቤ ቆማችሁ ብትመለከቱ ምኞቴ ነበር፡፡ አሁን እያወራሁ ያለሁት ስለሰዎች አይደለም የሰዎችን ህይወት በሃጥያት፤በግድየለሽነት እና በበሽታ የያዘዉ ሴጣን ነዉ፡፡ ነገር ግን ፊታቸዉን ስትመለከቱሴይጣን ሊጋለጥ እንደሆነ እንዳወቀ ታያላችሁ እናም እንግዳ የሆነ ለዉጥ በሰዎች ፊት ሲመጣ ታያላችሁ ይህም ሰይጣን ሲፈራነዉ፡፡ የእግዚአብሔር መንፈስ ሰዎችን ነጻአዉጥቶ ሊያጋልጠዉ እንደሆነ ያዉቃል ለዛም ነዉ ይሔን መሰባሰባችንን አብዝቶየሚጠላዉ፡፡ ስሞች ሲጠሩ እና በሽታዎች ሲጋለጡ ሴይጣን ያን ይጠላዋል አሁን ይሄ ታዲያ ምንድን ነዉ ይህ የሰዎችን አእምሮማንበብ አይደለም ፤ በመንፈስ የሰዎችን አእምሮ ግንኙነትም አይደለም ወይም ጥንቆላም አይደለም ማወቅ የምችልበት መንገድ በመንፈስ ቅዱስ በኩል በሚገኝ መገለጥ ብቻ ነዉ፡፡ በርግጥ ስጋዊ የሆነ ሰዉ የፈለገዉን ነገር ብሎ ሊሰይመዉ ይችላልነገር ግን ይህ ከመንፈስ ቅዱስ ብቻ ነዉ፡፡

በአብያተ ክርስቲያናት መካከል የኢየሱስ ክርስቶስን መገለጥ የሚያሳየዉን ይሄን መጽሃፍሰይጣን የሚጠላበትን ሌላ ምክንያት ላሳያችሁ ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትናም ዛሬም እስከለዘላለም የማይለዉጥ እና ያዉ መሆኑንየስነመለኮት አጥኚዎች ከሚያዉቁት ከዘጠና ፐርሰንት በላይ ሙሉ በሙሉ

ያዉቃል እግዚአብሔር የማይለዋወጥ አምላክ እንደሆነ ሁሉበሚሰራዉም የአሰራር መንገድ ተለዋዋጭ እንዳልሆነ ያዉቃል (ማርቆስ16 ላይ ያሉት ምልክቶች የሚከተላት ቤተክርስቲያን) ጌታኢየሱስ የእኔ ቤተ ክርስቲያን ብሎ የሚጠራት በእግዚአብሔር ሃይል የተመሰረተችዉ የመጀመሪያይቷ በባለሀምሳቀን የተጀመረችዉንእዉነተኛ ቤተክርስቲያን እንደሆነች ሌላዉ ሁሉ ግን ሐሰተኛ እንደሆነ በደንብ ያዉቃል፡፡

አሁን ይሄን አስታዉሱ ክርስቶስ በእዉነተኛይቷ ቤተክርስቲያን የሐዋርያት ስራ መጽሃፍቅጥያ ናት ነገር ግን የራዕይ መጽሀፍ የክርስቶስ ተቃዋሚዉመንፈስ እንዴት ወደ ቤተክርስቲያን መጥቶ እንዳቆሸሻት፤በራድ ወይም ትኩስ እንዳትሆን እንዳደረጋት፤የተለመደ እና ሀይል የለሽእንዳደረጋት ያሳየናል፡፡ ሰይጣን እና ስራዉን ያጋልጣል (የእግዚአብሔርን ህዝብ ለማጥፋት እና የእግዚአብሔርን ቃል ለማቃለልእንዴት እንደሚሞክር ያጋልጣል) ወደ እሳት ባህር እስከሚጣልበት ጊዜም እንደዚህ ለመዋጋት ይሞክራል፡፡ ነገር ግን መቆምአይችልም፡፡ እዉነተኛይቷ ቤተክርስቲያን ምን እንደሆነች፤ለምን አላማ እንደቆመች እንዲሁም ታላላቅ ስራዎችን የምትሰራ እንደሆነችሰዎች እዉነተኛ መገለጥ ማግኘት ከቻሉ ስዉር ሰራዊት እንደምትሆን ሰይጣን ያዉቃል፡፡ ክርስቲያን ተብሎ በሚጠራዉ ቤተክርስቲያን አዉድ ዉስጥ ስላሉት ሁለትአይነት መናፍስት እዉነተኛ መገለጥ ካገኙ እና በእግዚአብሔር የመለየት መንፈስ የክርስቶስ ተቃዋሚን መንፈስ መቋቋም ከቻሉሰይጣን በቤተክርስቲያን ፊት ሀይል አልባ ይሆናል፡፡

በርግጥም ክርስቶስ በምድረበዳ ዉስጥ ማሸነፍ እንደቻለ ዛሬም በተመሳሳይ መልኩ መገታትይችላል አዎ ሰይጣን መገለጥን ይጠላል ነገር ግን እኛ ደግሞእንወደዋለን በህይወታችን በሚሆነዉ እዉነተኛ መገለጥ የገሀነም ደጆች ሊቋቋሙን አይችሉም ነገር ግን እኛ በላያቸዉ ላይእንቋቋመዋለን፡፡

አስቀድሜ መጀመሪያ አካባቢ ላይ ለመናገር እንደሞከርኩት ይህ እያጠናነዉ ያለነዉመጽሃፍ በቤተክርስቲያን ዉስጥ እና ወደ ፊት ባለት ዘመናት የሚሰራቸዉ ስራዎች እና የእራሱ የኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥን ነዉ

መገለጡን ለማግኘት መንፈስ ቅዱስ የግድ ያስፈልገናልአለበለዚያ ግን መገለጡን ማግኘት አንችልም በማለት ለመግለጽ ሞክሪያለሁ ሁለት የተለያዩ ሃሳቦችን አምጥቶ የዚህ መጽሀፍ እዉነታላይ ለመድረስ አካል እንዲለብስ ለማድረግ የመንፈስቅዱስ ስራ ያስፈልገናል ያ ማለት ይሄ መጽሃፍ ለተለዩ ሰዎች ብቻ እንጂለማንኛዉም ሰዉ ሊገለጥ አይችልም፡፡

ትንቢታዉ እይታ ያለዉ ሰዉ መሆን ይጠይቃል ከእግዚአብሔርመስማትን ይጠይቃል ዝምብሎ እንደ አንድ ተማሪ ከአንድ ጥቅስ ወደ ሌላ ጥቅስ ማገላበጥ ብቻ አይደለም ምንም እንኳን ያ መልካምቢሆንም ነገር ግን ሚስጢር የመንፈስ ቅዱስ ትምህርት ያስፈልገዋል ካልሆነ ግን መቼም ግልጽ ሊሆን አይችልም፡፡ እንዴትከእግዚአብሔር ማድመጥ እንደምንፈልግ ራሳችንን ሙሉ በሙሉ ክፍት ማድረግ እና ለመንፈስ መሸነፍ እና ማወቅ ያስፈልጋል፡፡

ቀደም ሲል እንዳልኩት ይህ መጽሀፍ(የራዕይ መጽሃፍ) መጽሃፍ ቅዱስን ሙሉ በሙሉ መረዳት ማለት ነዉ የተቀመጠዉም በመጨረሻዉየመጽሃፍ ቅዱስ ክፍል ነዉ፡፡ ስለዚ አሁን ለምን የትንቢቱን ቃል የሚያነበዉ ወይም የሚሰማዉ የተባረከ ነዉ እንዳለታዉቃላችሁ፡፡ በዲያብሎስ ላይ ስልጣንን የሚሰጣችሁ የእግዚአብሔር መገለጥ ነዉ እናም ከዚህ መጽሃፍ ላይ የሚጨምሩም ሆነየሚቀንሱ ለምን የተረገመ ይሁን እንደሚል ማየት ትችላላችሁ፡፡

በርግጥም እንዲህ መሆን አለበት ፍጹም ከሆነዉከእግዚአብሔር መገለጥ ተጨምሮ እና ተቀንሶ እንዴት ጠላትን ማሸነፍ ይቻላል ያን ያህል ቀላል ነዉ ከቃሉ መገለጥ ዉጪ መቋቋምየሚቻልበት አንዳችም ነገር አይኖርም

ተመልከቱ ቁጥር 3 ላይ ለዚህ መጽሃፍ የተለየ ትኩረትለሚሰጡ በረከት እንዳለዉ ተገልጿል ይህ ደግሞ በብሉይኪዳን ዘመን የነበሩ ካህናት በማለዳ ለጉባኤዉ የሚያነቡትን ልማድሊያመላክት ይችላል አያችሁ ከካህናቱ በቀር ብዙዎች ማንበብ አይችሉም ስለሆነም ካህናቱ የግድ ያነቡላቸዉ ነበር ምንም ይሁንምንም የተነበበዉ ቃሉ እሰከሆነ ድረስ በረከት ነበረዉ፡፡

"ጊዜዉ አሁን ነዉ." ከዚ ቀደም ጊዜዉ አልደረሰምነበር ይሄ ታላቅ መገለጥ በእግዚአብሔር ጥበብ እና እዉቀት (ምንም እንኳን ሙሉ በሙሉ የታወቀ ቢሆንም) እስከ አሁን ድረስ ግንአልመጣም ነበር፡፡ ስለዚህ አንድ መመሪያን እንማራለን - ለእያንዳንዱ ዘመን የእግዚአብሔር መገለጥ ለዛ ዘመን ብቻ የሚገለጥመሆኑን፡፡

የእስራኤልን ታሪክ ተመልከቱ ለሙሴ የእግዚአብሔር መገለጥየመጣዉ በታሪክ ዉስጥ በአንድ በተወሰነ ጊዜ ብቻ እሱንም ህዝቡ ወደ እግዚአብሔር ባለቀሰ ሰአት ነበር ኢየሱስ እራሱ የሙላተመለኮት መገለጥ ሆኖ የመጣዉ ጊዜዉ በደረሰ ሰአት ነበር

በዚህም ዘመን(በሎዶቂያ) የእግዚአብሔር መገለጥ በራሱ በተቀጠረለት ጊዜ ይመጣል ፈጥኖም አይደለም ያለጊዜዉም አይደለምይሄንን አስቡና አሁን ያለንበትን የመጨረሻ ዘመን ቆጥራችሁ ድረሱበት፡፡

**ሰላምታ**

ራእይ 1:4-6,"ዘመኑ ቀርቦአልናየሚያነበዉ የትንቢቱን ቃል የሚሰሙትና በዉስጡ የተጻፈዉን የሚጠብቁት ብጹዓን ናቸዉ፡፡

4 - 5 ዮሐንስ በእስያ ላሉት ለሰባቱ አብያተክርስቲያናት ካለዉና ከነበረዉከሚመጣዉም በዙፋኑም ፊት ካሉት ከሰባቱ መናፍስት ከታመነዉም ምስክር ከሙታንም በኩር የምድርም ነገስታት ገዥ ከሆነ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን ለወደደን ከሃጢያታችንምበደሙ ላጠበን 6 መንግስትም ለአምላኩ ና ለአባቱም ካህናት እንድንሆን ላደረገ ለእርሱ ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ክብርና ኃይልይሁን አሜን፡፡."

እስያ የሚለዉ ቃል አነስተኛዋ እስያ ነዉ የኢንድያናንመጠን የምታህል ትንሽ ቁራሽ መሬት ነች ከሌሎቹ ቤተክርስቲያናት በተለየ መልኩ ሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት ከዚ ስፍራየተመረጡበት ምክንያት ባላቸዉ ባህሪያት ነዉ ከመቶ አመታት በኋላም በተመሳሳይ መልኩ በመጪዎቹ ተከታታይ ዘመናት ላይ የሚታይባህሪ ነበር፡፡

ከዙፋኑ ፊት ያሉት ሰባቱ መናፍስት እያንዳንዱ በነሩበትዘመን አገልግሎትን የሚሰጣቸዉ በሰባቱ መልእክተኞች ዉስጥ ሆኖ የሚሰራዉ መንፈስ ነዉ፡፡

አሁን እነዚህ ሁሉመገለጫዎች "ያለ," እና "የነበረ,"እና "የሚመጣ," እና "የታመነ ምስክር" እና "ከሙታንም በኩር," እና "የምድርም ነገስታት

ገኘከሆነ,” እና “አልፋና ዖሜጋ,” እና “ሁሉን ቻይ,”እነዚህ ሁሉመገለጫዎች የአንዱ እና የአንዱ አካል የሆነዉ ሀጥያታችንን ሁሉበገዛ ደሙ ያጠበን የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ስያሜዎች እና መገለጫዎች ናቸዉ።

በዮሃንስ ላይ የነበረዉየእግዚአብሔር መንፈስ በዚህ መልኩ የገለጸበት ምክንያት ከሁሉ በላይ የሆነዉን የኢየሱስ ክርስቶስን መለኮትነት እና የሙላተመለኮት አንድ አምላክነትን ለመግለጥ ነዉ። ዛሬ ዛሬ ከአንድ በላይ ሶስት አምላክ አለ የሚል የጅምላ ስህተት አለይሄ መገለጥለዮሃንስ በራሱ በኢየሱስ አማካኝነት ሲሰጠዉ ይሄንን ስህተት ያስተካክለዋል ሶስት አማላክ ሳይሆን በሶስት የተለያዩ ተግባራትየተገለጠ አንድ አምላክ ነዉ አብ፤ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ በሚል ስያሜ ያለ አንድ አምላክ አለ። የቀድሞዋ ቤተክርስቲያንየነበራት መገለጥ ይሄ ነበር ስለሆነም አሁን ባለንበት ዘመንም ከትክክለኛዉ የዉሃ አጠማመቅ ቀመር ጋር ተያይዞ መቃናትአለበት።

አሁን አሁን ዘመናዊየስነመለኮት አጥኚዎች በታዋቂ የክርስቲያን መጽሄቶች ላይ እንደተጻፈዉ ከእኔ ጋር አይስማሙም የስላሴ አስተምህሮት በዋናነት በብሉይኪዳን እንደተገለጸ ሁሉ በግልጽ ሁኔታ በአዲስ ኪዳን ዋና አስተምህሮት ላይም እናገኘዋለን። ከአንድ በላይ አምላክ በሚለዉጉዳይ ላይም የአዲስ ኪዳን መጽሃፍ ከብሉይኪዳን መጽሃፍ ላይ ከተገለጠዉ በላይ በደንብ ይቃወማል ።

ሆኖም ግን አዲስ ኪዳን ላይ እኩል ግልጽ በሆነ መልኩ አብ አምላክ እንደሆነ ፤ ልጅአምላክ እንደሆነ፤ መንፈስ ቅዱስ አምላክ እንደሆነ ያስተምራል እናም እነዚህ ሶስቱ የአንድ አካል መገለጫዎች ሳይሆኑ አንዳቸዉ ከሌላኛዉ ጋር በእዉነተኛ ዝምድና ዉስጥ የቆሙ ሶስት ራሳቹዉን የቻሉ አካሎች ናቸዉበሚል አስተሳሰብ ደግሞ በሶስት አካል ዉስጥ የሚኖር አንድ አምላክ የሚል የታወቀ አስተምህሮት አለ፡

የስላሴ አስተምህሮት ታላቁሚስጥርም በመጽሃፍ ቅዱስ ዉስጥ ያለዉ አምላክ በሶስት አካል ዉስጥ የሚኖር አንድ አምላክ መሆኑ ነዉ ይላሉ።

በርግጥ ሶስት አካል ያለዉ አንድ አምላክ እንዴት ሊኖርይችላል?በመጽሃፍ ቅዱስ ዉስጥእንዲህ አይነት አስተምህሮት የሚደግፍ ነገር አለመገኘቱ ብቻ ሳይሆን በአእምሮ እንኳን ምክንያታዊነት የጎደለዉ አስተሳሰብእንደሆነ ያሳያል ሶስት የተለያዩ አካላት፤ ተመሳሳይ ማንነት ያላቸዉ ሶስት አማልክት ይሆናሉ እንጂ ቋንቋ ትርጉሙን ካላጣበስተቀር አንድ አምላክ ሊሆኑ አይችሉም።

አስኪ እነዚህን ቃላቶችበደንብ አድምጧቸዉ “አልፋ እና ኦሜጋ፤ መጀመሪያ እና መጨረሻ፤ ያለ፤የነበረ ፤የሚመጣ ሁሉን ቻይ እኔ ነኝ።”ይህ አምላክ ነዉ። አንድነብይ የሆነ ሰዉ ብቻ የተናገረዉ አይደለም ይህ አምላክ ነዉ። የሶስት አምላኮች መገለጥም ሳይሆን ሁሉን ቻይ የሆነዉ የአንድ አምላክ መገለጥ ነዉ።

በመጀመሪይቷ ቤተክርስቲያን በሶስት አምላክ አልነበረም የሚያምኑት በሐዋሪያቱ መካከል እንዲህ ያለ እምነት ያለዉ አታገኙም እንዲህ ያለዉ አስተምህሮት እና ስጋዊ የሆነ አስተሳሰብ የተነሳዉ ሐዋርያቱ ካለፉ በኋላኒቂያ ተብሎ ከሚታወቀዉ ጉባዔ ጀምሮ ነዉ።

የሙላተ መለኮት አስተምህሮት በኒቂያ ጉባዔ ሁለትየተለያዩ ጽንፍ የያዙ ሃሳቦችን አስነሳ አንደኛዉ በብዙ አምላክነት የሚያምን ጽንፍ በሶስት አምላክ የማመን ጽንፍ ሲሆን ሌላኛዉአንድ አምላካዊነት ነዉ ነገር ግን ለዮሃንስ በመንፈስ አማካኝነት ለቤተክርስቲያን የመጣዉ መገለጥ “እኔ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስሁሉ በሁሉ የሆንኩ ነኝ ሌላ አምላክ የለም የሚል ነዉ።”ማህተሙንም በዚህ መገለጥ ላይ አደረገዉ።

አስኪ ይሄን ነገር ከግምት ዉስጥ አስገቡት የኢየሱስ አባት ማን ነበር? ማቴ፡1፡18 “ከመንፈስ ቅዱስ ጸንሳተገኘች” ይላል ኢየሱስ እራሱ ደግሞአግዚአብሄር አባቱ እንደሆነ ይናገራል እንዲህ ከሆነ ደግሞ ከላይ በተገለጸዉ መሰረት ከሄድን እግዚአብሔር አብ እና እግዚአብሔርመንፈስ ቅዱስ አንድ መንፈስ እንደሆነ ያሳያል በርግጥም ልክ ነዉ ካልሆነ ግን ኢየሱስ ሁላት አባቶች አሉት ልንል ነዉ በሌላቦታ ደግሞ አስተዉሉ ኢየሱስ እኔ እና አብ አንድ ነን ይላል ሁለት አይደለም አንድ ይሄም አንድ አምላክ እንደሆነ ያሳያል።

ይሄ ጉዳይ በታሪክም ሆነ በመጽሃፍ ቅዱስ እዉነት ቢሆንም ሰዎች ሶስት የሚባለዉ ነገርከየት እንደመጣ ይደነቃሉ ክርስቶስ ከሞተ በኋላ በ325 አመት የኒቂያ ጉባዔ ከተካሄደ ጀምሮ ነበር መሰረተ እምነት ሆኖየተጀመረዉ ይህ ስላሴ (በመጽሃፍ ቅዱስ ዉስጥ ፈጽሞ የማይገኝ ቃል) የሮማዊያንን ብዙ አማልክት መሰረት ያደረገ ነዉ።ሮማዊያን ጸሎት የሚጸልዩላቸዉ ብዙ አማልክት ነበራቸዉ።

ለቅድሚያ አያቶቻቸዉም እንደአማላጅ እንዲሆኑላቸዉ ወደእነሱ ይጸልያሉ። ለአማልክቶቻቸዉ አዲስ ስም የመስጠት ጅማሬ መሆኑ ነዉ። የበለጠ መጽሃፍ ቅዱሳዊ ለማድረግ ደግሞ የቅዱሳንምስም አለበት ጁፒተር፤ቬኑስ፤ማርስ በማለት ፈንታ ጳዉሎስ፤ጴጥሮስ፤ፋጢማ፤ክርስቶፎር ... የመሳሰሉትን ስያሜዎች ይጠቀማሉ የጣኦታዊነትአምልኳቸዉ አንድ አምላክ በሚል ብቻ ሊሰራላቸዉ ስላልቻለ ለሶስት ከፋፈሉት ልክ እንደ ቅድመ አያቶቻቸዉ የቅዱሳን አማላጅነትን እንዲሆን አደረጉ ከዛ ጊዜ አንስቶም ሰዎች በሶስት መልኩ የተገለጠ አንድ አምላክ ብቻመሆኑን ማስተዋል አቃታቸዉ።

እንደመጽሃፍ ቅዱስ አንድአምላክ ብቻ እንዳለ ያዉቃሉ ነገር ግን አስደናቂ የሆነ አስተምህሮት ለማስመሰል እግዚአብሔር በአንድ የወይን ዘለላ ወይም ጭብጥዉስጥ እንዳለ በእኩል መለኮትነት ያለ ሶስት አካል ያለዉ አምላክ ነዉ ይላሉ ። ነገር ግን ራእይ ላይ በግልጽ እንደሚናገረዉኢየሱስ ያለ፤የነበረ፤ የሚመጣ እሱ አልፋ እና ኦሜጋ ነዉ ይላል ማለትም ከ ሀ እስከ ፐ ሁሉ በሁሉ ነዉ ማለት ነዉ እሱ ሁሉንቻይ የሆነ ሁሉ በሁሉ የሆነ አምላክ ነዉ። እሱ የሳሎን ጽጌሬዳ፤ የቆላአበባ፤የንጋት ኮከብ፤ የጽድቅ ዛፍ፤ አባት፤ ልጅ እናመንፈስ ቅዱስ ነዉ። እርሱ አምላክ ነዉ። ሁሉንቻይ የሆነ አምላክ አንድ አምላክ ነዉ።

1ኛጢሞቲዮስ 3፡16 እንዲህ ይላል “እግዚአብሔርን የመምሰልሚሲጢር ያለ ጥርጥር ታላቅ ነዉ፤ በሥጋ የተገለጠ፤በመንፈስ የጸደቀ፤ ለመላእክት የታየ፤በአህዛብ የተሰበከ በአለም የታመነበክብር ያረገ”መጽሐፍ ቅዱስ የሚናገረዉ ይሄን ነዉ እዚህ ላይ አንደኛ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ አካል ብሎአይናገርም። የሚለዉ እግዚአብሔር በስጋ የተገለጠ አንድ አምላክ መሆኑን ነዉ ያ ሁሉን ነገር ይደመድመዋል አምላክ እራሱ ስጋንለብሶ መጣ ይሄ ሌላ አካል ያለዉ አምላክ አያስኘዉም እራሱ አምላክ ነዉ ስለዚህ ይሄ ያኔም የመገለጥ ጉዳይ ነዉ አሁንምየመገለጥ ጉዳይ ነዉ አንድ አምላክ።

ወደ መጽሃፍ ቅዱስእንመለስና ከጅማሬዉ ስለራሱ በገለጠበት መልኩ እንየዉ ታላቁ ያህዌ በእሳት አምድ ምሳሌ እንደ ቃል ኪዳን መላእክ በእሳት አምድ ዉስጥ በመኖር እና የእስራኤልንህዝብ እለት እለት በመምራት ተገለጠ። በቤተመቅደስ መምጣቱን በታላቅ ደመና በመታየት አሳወቀ። አንድ ቀን ግን ከድንግል በተወለደ በተዘጋጀለት አካል ተገለጠእስራኤላዊያን ካዘጋጁለት የቤተመቅደስ ድንኳን በላይ የሆነዉ አምላክ አሁን በሰዎች መካከል እራሱን በሰዉ ስጋ በተሰራ ቤተመቅደስ አኑሮ ተመላለሰ። ነገር ግን ያ እራሱ አምላክ ነበር።

መጽሃፍቅዱስ እግዚአብሔር በክርስቶስ ዉስጥ እንዳለያስተምራል አካሉ ኢየሱስ ነዉ በአካሉም የእግዚአብሔር ሙላት ነበረበት ከዚ ሌላ ግልጽ የሆነ ነገር የለም ሚስጥር ነዉ አዎነገር ግን እዉነታዉም ይህ ነዉ ስለዚህ ቀድሞም ሶስት አካል አልነበረም አሁንም ያዉ ነዉ ተመሳሳይ አንድ አምላክ እናም ይሄዉአንዱ አምላክ በስጋ ተገለጠ፡፡

ኢየሱስ እንዲህ አለ “ከእግዚአብሔር ወጥቻለሁ ወደ እግዚአብሔርም እመለሳለሁ” ዮሀንስ 16፡27-28 ያነዉ በትክክል የተከናወነዉ፡፡ በሞት፤በመቀበር፤ከሞት በመነሳት እና በማረግ መልክ ከምድር የነበረዉን ቆይታ ተወገደ ጳዉሎስበደማስቆ መንገድ ላይ አገኘዉና ኢየሱስ ለጳዉሎስ እንዲህ አለዉ “ሳኦል ሳኦል ሆይ ስለምን ታሳድደኛለህ?”ጳዉሎስም መልሶ “ጌታ ሆይ አንተ ማን ነህ ?”ሲለዉ “እኔ ኢየሱስ ነኝ” ብሎ መለሰለት እርሱየሚያሳዉር የእሳት አምድ ነበር፡

ተመልሼ እመጣለሁ እንዳለ እንዳዛዉ አደረገ በዚህ የስጋ ቤተመቅደስ በሰዉ አካል ከመገለጡ አስቀድሞ ወደነበረበት ማንነት ተመለሰ ያን ነበር ዮሀንስ የተመለከተዉ ዮሃንስ 1፡18 “እግዚአብሔርን ያየ አንድ ስንኳ የለም በአባቱ እቅፍያለዉ አንድያ ልጁ ተረከዉ እንጂ” እዚህ ጋር አስተዉሉ ዮሀንስ ኢየሱስ ብሎ ሲናገር በአባቱ እቅፍ ያለዉን ኢየሱስን ነዉ፡፡

ሉቃ 2፡11 እንዲህ ይላል “እነሆ በዳዊት ከተማ አዳኝ የሆነዉ ክርስቶስ ጌታተወልዶላችኋልና”ክርስቶስ ሆኖ ተወለደ ከስምንት ቀናት በኃላም በሚገረዝበት ቀን ኢየሱስ የሚል ስም ተሰጠዉልክ መልአኩ እንደተናገረዉ እኔ ብራንሃም ሆኜ ተወልጃለሁ የተወለድኩ ቀን ደግሞ ዊልያም የሚል ስም ተሰጠኝ እርሱ ክርስቶስነበር በሰዎች መካከል ሲወርድ ግን ስም ተሰጠዉ ያ የተገለጠዉ የሚታየዉ የሰዉ ቤተ መቅደስ ኢየሱስ ተብሎ ተጠራ፡፡ እርሱ የክብር ጌታ ነዉ፤በስጋ የተገለጠ ሁሉን ቻይ ነዉ፤እርሱእግዚአብሔር አባት፤ልጅ እና መንፈስ ቅዱስ ነዉ፡፡ እርሱ ሁሉንም ነዉ፡፡

አባት፤ልጅ እና መንፈስ ቅዱስ ስያሜዎች ናቸዉ ስሞችአይደሉም ለዛም ነዉ በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ስም የምናጠምቀዉ ስሙ ያ ስለሆነ ስያሜ አይደለም የእነዚህ ስያሜዎች ስም ነዉ ልክአዲስ የተወለደን ልጅ አንስታችሁ ስም እንደምትሰጡት ልጅ የሆነዉነገር ነዉ ልጅ ስያሜ ነዉ ከዛም ስም ትሰጡታላችሁ ጀን ሔንሪብራዉን “በኢየሱስ ስም” ብቻም አታጠምቁም በአለም ላይ ኢየሱስ ተብለዉ የሚጠሩብዙ ሺህ ሰዎች አሉና አዳኝ የሆነዉ ኢየሱስ ከመምጣቱም አስቀድሞ ነበሩና ክርስቶስ ሆኖ የተወለደዉ ግን አንድ ብቻ ነዉ “ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ”

ሰዎች ኢየሱስ ዘላለማዊ የሆነ የእግዚአብሔር ልጅ ብለዉ ያወራሉ አሁን ይሄ እርስ በእርሱ አይጋጭም?“ልጅ” የሚል ነገር የሰማ ሁሉ ዘላለማዊ ሊሆን ይችላል?ልጅነት ጅማሬ አለዉ ነገር ግን ዘላለማዊ የሆነዉ እርሱ ጅማሬ የለዉም እርሱ በስጋ የተገለጠ ያህዌ የሆነዉዘላለማዊ አምላክ ነዉ

በዮሃንስ ወንጌል ላይ እንዲህ ይላል “በመጀመሪያ ቃል ነበር ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበርቃልም እግዚአብሔር ነበር ”ቃልም ስጋን ለብሶ በመካከለቻን አደረ“ዘላለማዊ ለሆነዉ ለአባቱ ቃል እዉነተኛ እና ታማኝ ምስክር ነበር ነብይ ነበር አባቱእንዲናገር ያዘዘዉንም ተናገረ እርሱም እንዲህ አለ ”አብ በእኔ ዉስጥ ነዉ“ ይህ ቤተ መቅደስ የሆነዉ ኢየሱስ የተናገረዉ ነዉ ”አብ በእኔ ዉስጥ ነዉ“

እግዚአብሔር ብዙ ስያሜዎች አሉት የእኛ ጽድቅ እናየእኛ ሰላም እና በሁሉ ስፍራ የሚገኝ እና አባት እና ልጅ እና መንፈስቅዱስ ነገር ግን አንድ የሰዉ ስም አለዉ ያም ስምኢየሱስ ነዉ፡፡

እግዚአብሔር ሶስትመገለጫዎች አልያም ሶስት አገልግሎቶች ስላሉት ግራ እንዳያጋባችሁ በምድር ላይ ነብይ ነበር በሰማይ ካህን ነዉ ወደ ምድርተመልሶ ሲመጣ የነገስታት ንጉስ ነዉ “ያ የነበረዉ ”- ነብይ ኢየሱስ “ያ ያለዉ” እርሱ ካህናችን የማማለድንስራ የሚሰራልን የእኛን ስሜት የሚሰማዉ “ያ የሚመጣዉ” - መጪዉ ንጉስ በምድር ላይ ቃል ነበር ነብይ ሙሴ ስለ እርሱ እንዲህ አለ “ጌታ አምላካችሁ እንደእኔያለ ነብይ ያስነሳል የነብዩን ቃል የማይሰማ ሁሉ ከህዝቡ መካከል ይቆረጣል”

አስተዉሉ እነዚህን ስለ ኢየሱስ ያሉ እዉነታዎች በምድርላይ ነብይ፤በግ እና ልጅ ነበር እነዚህ በራሱ ሶስትአያደርጉትም ነገር ግን የአንዱ ኢየሱስ መገለጫዎች ወይም አገልግሎቶች ናቸዉ፡፡

የስላሴ አስተምህሮትተከታዮች በሙላተ መለኮት ዉስጥ ከአንድ በላይ ሶስት አካላት አሉ ለማለት እንደማረጋገጫ የሚጠቀሙበት የመጽሃፍ ቅዱስ ክፍል አለራእይ 5፡6-8

> *“በዙፋኑና በአራቱ እንስሶች መካከልምበሽማግሌዎች መካከልም እንደ ታረደ በግ ቆሞ አየሁ ሰባትም ቀንዶች እና ሰባት ዓይኖች ነበሩት እነርሱም ወደ ምድር ሁሉ የተላኩየእግዚአብሔር መናፍስት ናቸዉ፡፡ መጥቶም በዙፋኑ ላይ ከተቀመጠ ከዚያ ከቀኝ እጁ መጽሐፉን ወሰደዉ፡፡ መጽሐፉንም በወሰደ ጊዜአራቱ እንስሶችና ሃያ አራቱ ሽማግሌዎች በበጉ ፊት ወደቁ እያንዳንዳቸዉም በገናንና የቅዱሳን ጸሎት የሆነ ዕጣን የሞላበትንየወርቅ ዕቃ ያዙ፡፡”*

በርግጥ እነዚህ ጥቅሶች ተነጣጥለዉ ከታዩ አስተምህሮታቸዉን የሚያረጋግጥላቸዉ ይመስላሉአስተዉሉ ግን ያልኩት ጥቅሶቹ ተነጣጥለዉ ከታዩ ነዉ፡፡ ሆኖም ግን ራእይ4፡2-3 እና 9-11 አንብቡት

> *“ወዲያዉ በመንፈስ ነበርሁ እነሆም ዙፋን በሰማይቆሞአል በዙፋኑም ላይ ተቀማጭ ነበረ፡፡ ተቀምጦም የነበረዉ በመልኩ የኢያስጲድንና የሰረርዲን ዕንቁ ይመስል ነበር በመልኩምመረግድን የመሰለ ቀስተ ደመና በዙፋኑ ዙሪያ ነበረ፡፡” “እንስሶቹም በዙፋን ላይ ለተቀመጠዉ ከዘላለም እስከዘላለም በሕይወት ለሚኖረዉ ለእርሱ ክብርና ዉዳሴ ምስጋናም በሰጡት ጊዜ ሃያ አራቱ ሽማግሌዎች በዙፋን ላይ በተቀመጠዉ ፊትወድቀዉ ከዘላለም እስከ ዘላለም በሕይወት ለሚኖረዉ እየሰገዱ ጌታችን እና አምላካችን ሆይ አንተ ሁሉን ፈጥረሃልና ስለ ፈቃድህምሆነዋልና ተፈጥረዉማልና ክብር ዉዳሴ ሀይልም ልትቀበል ይገባሃል እያሉ በዙፋኑ ፊት አክሊላቸዉን ያኖራሉ፡፡ ”*

ቁጥር2 የሚለዉን በጥንቃቄ አስተዉሉት በዙፋኑ ላይ የተቀመጠዉ “አንድ” (ሁለት ወይም ሶስት አይልም ነገር ግንአንድ) ቁጥር3 እንዲህ ይላል እንደ ኢያስጲድን ድንጋይ የሚመስለዉን ቀና ብለዉ ተመለከቱት “እርሱን” እንጂ (እነርሱን አይደለም) ቁጥር9 እንዲህ ይላል አራዊቶቹ ክብርን ሰጠት “ለእርሱ” እንጂ ለእነርሱ አይደለም ቁጥር10 ላይ እንዲህ ይላል ሽማግሌዎቹ በፊቱ ሰገዱ “ለእርሱ” እንጂ ለእነርሱ አይደለም ቁጥር11 ላይ እንዲህ ይላል ጌታ ሆይ ይገባሃልና ብለዉ አለቀሱ “ጌታ” እንጂ ጌቶች አይልም በዛዉ ቁጥር11 ላይ እንዲህ ይላል ይህ በዙፋኑ ላይ የተቀመጠዉ “ፈጣሬ” ነዉ ያም ኢየሱስ ነዉ (ዮሃ1፡3)የብሉይኪዳኑ ያህዌ መንፈስ የሆነዉ አምላክ (ዘፍጥረት 1፡1)

እዚህ ላይ ብቻ ግን አናቆምም ራዕይ 3፡21እንብቡት"እኔ ደግሞ ድል እንደነሳሁ ከአባቴም ጋርበዙፋኑ ላይ እንደተቀመጥሁ ድል ለነሳዉ ከእኔ ጋር በዙፋኔ ላይ ይቀመጥ ዘንድ እሰጠዋለሁ፡፡" እንዲሁም እብራዊያን 12፡2 እንብቡት "የእምነታችንንም ራስና ፈጻሚዉን ኢየሱስንተመልክተን በፊታችን ያለዉን ሩጫ በትእግስት እንሩጥ እርሱ ነዉርን ንቆ በፊቱም ስላለዉ ደስታ በመስቀል ታግሦ በእግዚአብሔርቀኝ ተቀምጧልና፡፡"

ይሄን አስተዉሉ እራሱ ኢየሱስ እንዳለዉ የራእይ መጽሃፍን እንደጻፈ እራሱ በአባቱ ዙፋንላይ ተቀምጫለሁ አለ በጳዉሎስ ላይ የነበረዉ መንፈስ (እራሱ የክርስቶስ መንፈስ በትንቢት መንፈስ የመጣዉ ቃል) እርሱ በአብቀኝ ተቀመጠ አለ ነገር ግን ደግሞ ዮሃንስ በዙፋኑ ላይ ያለዉን ሲመለከት በዙፋኑ ላይ የተቀመጠዉ "አንድ" ብቻ ነዉ ከራእይ 4፡2-3በጊዜ ሂደት ተከትሎ ራእይ 5፡6-8 ያለዉን የምናየዉ በራእይ4፡2-3 እና 9-10 እንደተጠቀመዉ "በጉ" በዙፋኑ ላይ ከተቀመጠዉ"ከእርሱ" መጽሃፉን ሲወስድእንመለከተዋለን ታዲያ ይሄ ምንድን ነዉ? የአንዱ አምላክ ሚስጢር እርሱ (ኢየሱስ) ከእግዚአብሔር መጣ በስጋ ተገለጠ፤ ሞተ፤ሞትንም ድል አድርጎ ተነሳ እናም ወደ አባቱ እቅፍ ተመለሰ ዮሃንስ እንደገለጸዉ በአባቱ እቅፍ ያለዉ አንድያ ልጁ ተረከዉዮሃ1፡18 አሁን እግዚአብሔር (መሲሁ) ሙሽራይቱን የሚወስድበት እና እራሱን ለእስራኤላዉያን የሚገልጥበት የሚያሳዉቅበት ጊዜነዉ

"የዳዊት ልጅ፤ የነገስታትንጉስ ፤ የጌቶች ጌታ እና የአህዛብ ሙሽራይት ሙሽራ" በመሆን እግዚአብሔር ዳግም አካላዊ ህብረትን ለመፍጠርእንደሚመጣ እናያለን ይሄ "ሁለት" አምላክ አይደለም ነገርግን እራሱን በሶስት ታላላቅ ስያሜ እና አገልግሎቶች የገለጠ አንድ አምላክ እንጂ

ህዝቡ ነብይ እንደሆነ ያዉቃል የመሲሁም ምልክቶች ሁሉ በነብይ በኩልእንደሚፈጸም ያዉቃሉ ዮሃ፡44-52

*"ፊሊጶስም ከእንድርያስ እና ከጴጥሮስ ከተማ ከቤተ ሳይዳ ነበረ፡፡ ፊሊጶስ ናትናኤልን አግኝቶ ሙሴ በሕግነቢያትም ስለ እርሱ የጻፉትን የዮሴፍን ልጅ የናዝሬቱን ኢየሱስን አግኝተነዋል አለዉ፡፡ ናትናኤልም፡፡ ከናዝሬት መልካም ነገርሊወጣ ይችላልን አለዉ፡፡ ፊሊጶስ መጥተህ እይ አለዉ፡፡ኢየሱስ ናትናኤልን ወደ እርሱ ሲመጣ አይቶ ተንኮል የሌለበት የእስራኤልሰዉ እነሆ አለ፡፡ ናትናኤልም ከወዴት ታዉቀኛለህ አለዉ ኢየሱስም መልሶ ፊሊጶስ ሳይጠራህ ከበለስ በታች ሳለህ አየሁህ አለዉ፡፡ ናትናኤልም መልሶ መምህር ሆይ አንተ የእግዚአብሔር ልጅነህ አንተ የእስራኤል ንጉስ ነህ አለዉ፡፡ ኢየሱስም መልሶ ከበለስ በታች አየሁህ ስላልሁ አመንህን ከዚህ የሚበልጥ ነገርታያለህ አለዉ፡፡ እዉነት እዉነት እላችኋለሁ ሰማይ ሲከፈት የእግዚአብሔርም መላእክት በሰዉ ልጅ ላይ ሲወጡ እና ሲወርዱታያላችሁ አለዉ፡፡"*

የእግዚአብሔር ምርጦች መሲሁን እና የተቀባዉንየእግዚአብሔርን ቃል የሚያዉቁበት አንዱ መንገድ በሰዉ ልብ ዉስጥ የተሰወረን ሃሳብ ማወቅ መቻል ነዉ፡፡ እብራዊያን 4፡12

*"የእግዚአብሔር ቃል ሕያዉ ነዉና የሚሰራምሁለትም አፍ ካለዉ ሰይፍ ሁሉ ይልቅ የተሳለ ነዉ ነፍስንና መንፈስንም ጅማትንና ቅልጥምንም እስኪለይ ድረስ ይወጋል የልብንምስሜትና አሳብ ይመረምራል፡፡"*

በዉሃ መቅጫ ጉድጋድያገኛት ሰማራዊቷ ሴት በልቧ የተሰወረዉን ሃሳብ እንደገለጠ ስትሰማ ነብይ እንደሆነ አወቀች መሲሁም የተሰወረን ሃሳብየሚገልጥ የሚያዉቅ መሆኑን ጠቆመች፡፡

ዮሃንስ4፡7-26

*"ከሰማርያ አንዲት ሴት ዉኃ ልትቀዳ መጣች ኢየሱስም ዉኃ አጠጪኝ አላትደቀመዛሙርቱ ምግብ ሊገዙ ወደ ከተማ ሄደዉ ነበርና፡፡*

*ስለዚህ ሳምራዊቲቱ ሴት አንተ የይሁዳ ሰዉ ስትሆን ሳምራዊት ሴት ከምሆንከእኔ መጠጥ እንዴት ትለምናለህ አለችዉ አይሁድ ከሳምራዊያን ጋር አይተባበሩም ነበርና፡፡*

*ኢየሱስ መልሶ የእግዚአብሔርንስጦታና ዉኃ አጠጪኝ የሚልሽ ማን መሆኑንስ ብታዉቂ አንቺትለምኚዉ ነበርሽ የሕይወትንም ዉኃ ይሰጥሽ ነበር አላት*

*ሴቲቱ ጌታ ሆይ መቅጃ የለህም ጉድጓዱም ጥልቅ ነዉ እንግዲህ የሕይወት ዉሃ ከየት ታገኛለህ በእዉነት አንተ ይህን ጉድጓድ ከሰጠንከአባታችን ከያዕቆብ ትበልጣለህን ራሱም ልጆቹም ከብቶቹም ከዚህ ጠጥተዋል አለችዉ፡፡*

*ኢየሱስም መልሶ ከዚህ ዉኃ የሚጠጣ ሁሉ እንደገናይጠማል እኔ ከምሰጠዉ ዉኃ የሚጠጣ ሁሉ ግን ለዘላለም አይጠማም እኔየምሰጠዉ ዉኃ በእርሱ ዉስጥ ለዘላለም ህይወት የሚፈልቅ የዉኃ ምንጭ ይሆናል እንጂ አላት፡፡*

*ሴቲቱ ጌታ ሆይ እንዳልጠማ ዉኃም ልቀዳወደዚህ እንዳልመጣ ይህን ዉኃ ስጠኝ አለቸዉ፡፡ ኢየሱስም ሒጂ እና ባልሽን ጠርተሽ ወደዚህ ነይ አላት፡፡*

*ሴቲቱ መልሳ ባል የለኝምአለችዉ፡፡*

*ኢየሱስ ባል የለኝም በማለትሽ መልካም ተናገርሽ አምስት ባሎች ነበሩሽና አሁን ከአንቺ ጋር ያለዉ ባልሽ አይደለም በዚህስእዉነት ተናገርሽ አላት ሴቲቱ ጌታ ሆይ አንተ ነብይ እንደሆንህ አያለሁ፡፡*

*አባቶቻችን በዚህ ተራራ ሰገዱ እናንተም ሰዉ ሊሰግድበትየሚገባዉ ስፍራ በኢየሩሳሌም ነዉ ትላላችሁ አለችዉ፡፡*

*ኢየሱስም እንዲህ አላት አንቺ ሴት እመኚኝ በዚህ ተራራ ወይም በኢየሩሳሌምለአብ የማትሰግዱበት ጊዜ ይመጣል፡፡*

*እናንተስ ለማታዉቁት ትሰግዳላችሁ እኛ መዳን ከአይሁድ ነዉና ለምናዉቀዉ እንሰግዳለን፡፡ ነገርግን በእዉነት የሚሰግዱ ለአብ በመንፈስ እና በእዉነት የሚሰግዱበት ጊዜ ይመጣል አሁንም ሆኗል አብ ሊሰግዱለት እንደነዚህ ያሉትንይሻልና እግዚአብሔር መንፈስ ነዉ የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእዉነት ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል፡፡*

*ሴቲቱ ክርስቶስ የሚባል መሲሕእንዲመጣ አዉቃለሁ እርሱ ሲመጣ ሁሉን ይነግረናል አለችዉ፡፡ ኢየሱስ፡፡ የምናገርሽ እኔ እርሱ ነኝ አላት፡፡“*

ራእይ15፡3እንዲህ ይላል

*“ሁሉን የምትገዛ ጌታ አምላክ ሆይ ሥራህ ታላቅና ድንቅ ነዉ የአህዛብ ንጉስ ሆይ መንገድህ ጻድቅና እዉነተኛነዉ ጌታ ሆይ የማይፈራህና ስምህን የማያከብር ማን ነዉ አንተ ብቻ ቅዱስ ነህና የጽድቅም ስራህ ስለ ተገለጠ አሕዛብ ሁሉይመጣሉ በፊትህም ይሰግዳሉ እያሉ የእግዚአብሔርን ባሪያ የሙሴን ቅኔና የበጉን ቅኔ ይዘምራሉ፡፡”*

በራእይ 15፡3 ላይ እንዲህ ይላል አያችሁት በጉየካህናት አለቃ ደሙን ይዞ በምህረት ዙፋን ላይ ለሀጥያታችን ስርየት ተቀምጧል ሁሉን ቻይ የሆነዉ ጌታ፡፡ አሁን ላይ ያለዉአገልግሎቱ ይህነዉ፡፡ ከይሁዳ ነገድ የሆነዉ አንበሳ ለሀጥያታችን ስርየት ደሙን እየረጨ ነዉ፡፡ በሀይል እና በግርማ ንጉስ ሆኖለመግዛት ዳግም ይመጣል፡፡ የምድር ንጉስ ሆኖ ይመጣል፡፡ በርግጥ አሁን ንጉስ አይደለም አይልም እርሱ ንጉሳችን የቅዱሳን ንጉስነዉና በአሁን ሰአት መንፈሳዊ መንግስት ነዉ በዚህ አለም ስርአት ዉስጥ አይደለም ያለዉ ለዛም ነዉ እኛ በሁሉ ነገር ከአለምየምንለይበት ምክንያት ዜግነታችንም ሰማያዊ ነዉ፡፡ በህይወታችን የሚንጸባረቀዉም ኢየሱስ ንጉስ የሆነበትን የመንፈሳዊ አለምዉልደትን ነዉ፡፡

ለዛም ነዉ ሴቶቻችን የወንድ ልብስ የማይለብሱት ወይም ጸጉራቸዉንም የማይቆረጡት አልያምአለም አብዝቶ የሚወዳቸዉን ኮስሞቲክሶችም የማይጠቀሙት፡፡ ለዛም ነዉ ወንዶቻችን የማይጠጡት የማያጨሱት እና በሀጥያት የማይኖሩትየኛ ግዛት በዉስጣቻን በሚኖረዉ የክርስቶስ መንፈስ ሃይል በሃጥያት ላይ ገዥ መሆን ነዉ የትኛዉም በዚች ምድር ላይ ያለ ግዛትመንግስት ሁሉ ይወድቃል የኛ ግዛተ መንግስት ብቻ ቆሞ ይቀራል፡፡

የመጽሐፍ ቅዱስን ጥቅሶች እያጣቀስን የአንዱን እዉነተኛ አምላክ ክብር እና መገለጫዎችስናወራ ነበር ነገር ግን እርሱ መንፈሳዊ በሆነ መገለጥ እንጂ በአእምሮ ጥናት አይታወቅም፡፡ ይሄዉ እራሱ ኢየሱስ ከስጋመገለጡብኃላ ወደ ብርሃን እሳት አምድ ተመለሰ፡፡ ነገር ግን ዳግም ተመልሶ በመንፈስ አማካኝነት በህዝቡ መካከል እንደሚኖር የተስፋቃል ሰጥቷል እናም በባለ ሀምሳ በተባለ ቀን ያ የእሳት አምድ በእያንዳንዳቸዉ ላይ በተከፋፈሉ ልሳናት ወረደ፡፡

እግዚአብሔር ምን እያደረገ ነበር? ወደ ቤተክርስቲያን እራሱን ከፋፍሎ ለወንዱም ለሴቱም ድርሻ እየሰጣቸዉነበር ቀድሞ እንደተናገረዉ እራሱን ለቤተክርስቲያን ከፋፍሎ ሰጠ፡፡

ዮሃንስ14፡16-23“ብትወዱኝ ትእዛዜን ጠብቁ፡፡

*እኔም አብንእለምናለሁ ለዘላለምም ከእናንተ ጋር እንዲኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኃል፡፡*

*እርሱም አለም የማያየዉ እና የማያዉቀዉ ስለ ሆነ ሊቀበለዉ የማይቻለዉ የእዉነት መንፈስ ነዉ ነገር ግን ከእናንተ ዘንድ ስለሚኖር በዉስጣችሁም ስለሚሆን እናንተታዉቃላችሁ፡፡*

*ወላጆች እንደሌላቸዉ ልጆች አልተዋችሁም ወደ እናንተ እመጣለሁ፡፡*

*ገና ጥቂት ዘመን አለ ከዚህም በኃላ አለምአያየኝም እናንተ ግን ታዩኛላችሁ እኔ ሕያዉ ነኝ እና እናንተም ደግሞ ሕያዋን ትሆናላችሁ፡፡*

*እኔ በአባቴ እንዳለሁ እናንተምበእኔ እንዳላችሁ እኔም በእናንተ እንዳለሁ በዚያን ቀን ታዉቃላችሁ፡፡*

*ትእዛዜ በእርሱ ዘንድ ያለችዉ የሚጠብቃትም የሚወደኝእርሱ ነዉ የሚወደኝንም አባቴ ይወደዋል እኔም እወደዋለሁ ራሴንም እገልጥለታለሁ፡፡*

*የአስቆሮቱ ያይደለ ይሁዳም ጌታ ሆይ ለአለምሳይሆን ራስህን ልትገልጥ ያለህ እንዴት ነዉ?አለዉ፡፡*

*ኢየሱስም መለሰ አለዉም፡፡ የሚወደኝ ቢኖር ቃሌን ይጠብቃል አባቴም ይወደዋል ወደ እርሱም እንመጣለን በእርሱም ዘንድ መኖሪያእናደርጋለን፡፡“*

ምን ብሎ ተናገረ ሌላ አጽናኝ ወደሚልክላቸዉ አባቱእንደሚጸልይ ከእነርሱ(ከደቀመዛሙርቱ) ጋር ያለ በዉስጣቸዉ ግን ያልነበረ ያም ክርስቶስ ነዉ፡፡ ከዛም ቁጥር23 ስለራሱ እናስለ አባቱ ሲናገር እንመጣለን አለ እዚህ ጋር ነዉቁምነገሩ “አባት ሆኖ የተገለጠዉ፤ልጅሆኖ የተገለጠዉ ገና በብዙ መንገድ የሚገለጠዉ እራሱ የእግዚአብሔር መንፈስ መንፈሱ እየመጣ ነዉ” መንፈስ የሆነዉ አንዱ እግዚአብሔር

ለዚህ ነዉ ማንም ሰዉ መጥቶ ቅዱስ ሰዉ ጳጳስ የሆነ ወይም ቄስ ወይም እረኛ የሆነ ነዉማለት የማይችለዉ ቅዱስክርስቶስ ነዉ በዉስጣችን ያለዉ መንፈስ ቅዱስ ነዉ፡፡ የትኛዉ ባለስልጣን ነዉ በድፍረት ምእመኑ ምንምአይነት ቃል መናገር አይችልም የሚለዉ እያንዳንዱ ሰዉ የሚናገረዉ አለዉ፡፡ እያንዳንዱ ስራ አለዉ፡፡ እያንዳንዱ አገልግሎትአለዉ፡፡

በእያንዳንዱ ላይ እራሱን ከፋፍሎ በባለሀምሳ ቀን የመጣዉ መንፈስ ቅዱስ ክርስቶስ በዮሃ14፡20 ላይየተናገረዉ ይፈጸም ዘንድ ነዉ “እኔ በአባቴ እንዳለሁ እናንተም በእኔ እንዳላችሁ እኔም በእናንተ እንዳለሁ በዚያን ቀን ታዉቃላችሁ፡፡”

ታላቁ እኔ ነኝ ያለዉ ሁሉን ቻይ አምላክ እዉነተኛየሆነችዉን ቤተክርስቲያን ሊሞላት በመንፈስ መጣ ወደ ፈለገዉ ስፍራ ሁሉ የሚሄድ በሚፈልገዉ ሰዉ ላይ ሁሉ የማረፍ መብቱ አለዉበመካከላችን ቅዱስ ብለን የምናስቀምጠዉ ሰዉ የለም ነገር ግንእዉነተኛ ሆኖ የተሰበሰበዉ የጌታ ምእመን ሁሉ ከመንፈስ ቅዱስ መገኘት የተነሳ ቅዱስ ነዉ መንፈስ ቅዱስ የሆነዉ እሱ ነዉ ቅዱስየተሰበሰበዉ ምእመን በራሱ ቅዱስ አይደለም፡፡

አሁን ይህ መገለጥ ነዉ ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ ነዉ፡፡ የብሉይ ኪዳኑ ያህዌ የአዲስኪዳኑ ኢየሱስ ነዉ፡፡ የፈለጋችሁትን ያህል በትለፉ ብትሞክሩ ሶስት አምላክ አለ ብላችሁ ልታረጋግጡ አትችሉም፡፡ በርግጥ እርሱአንድ አምላክ እንደሆነ እዉነታዉ ይገባችሁ ዘንድ የመንፈስ ቅዱስ መገለጥ ያስፈልጋል፡፡

የብሉይ ኪዳኑ ያህዌ የአዲስ ኪዳኑ ኢየሱስ እንደሆነ ለማየት መገለጥ ያስፈልጋል ይህን እዉነት እንዳይመለከቱ ሰይጣን ሰዎችን ወደ ቤተ ክርስቲያን ገብቶአታሏል፡፡ በዚህ መልኩም ሲታለሉ ያን ያህል እሩቅ አልነበረም የሮማ ቤተክርስቲያን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ማጥመቅካቆመች በኋላ ነዉ

ብዙ ሊያደናብሩ የሚችሉየመጽሃፍ ቅዱስ ቃላት ባለንበት በእነዚህ ቀናቶች ስለ ሙላተ መለኮት ጉዳይ በርግጥ እዉነተኛ የሆነ የመንፈስ ቅዱስ መገለጥ እንደሚያስፈልግ አምናለሁ፡፡ ሆኖም ግን የቤተክርስቲያን የመቋቋሚያእና ማሸነፊያዋ የተመሰረተዉ በመገለጥ ላይ ብቻ ነዉ ስለሆነም ለሁላችንም እዉነቱን ይገልጥልን ዘንድ እግዚአብሔርንእንጠብቀዋለን፡፡

ሐዋርያቱ ከጌታ ቀጥተኛ ትእዛዝ ከሆነዉ በአብ፤በወልድእናበመንፈስ ቅዱስ ስም የማጥመቅ ትእዛዝ ትክክለኛ መንገድ ወጥቶ ለመሄድ ለደቂቃ እንኳን የሚችሉ ይመስላችኋል በፈቃዳቸዉ የማይታዘዙ? እነርሱ ስሙ ማን እንደሆነያዉቃሉ ደግሞም በመጽሐፍ ቅዱስ ዉስጥ ከጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ስም ዉጪ ያጠመቁበት አንዳች ቦታ አታገኙም፡፡

የሀዋርያት ስራ መጽሐፍ የቤተክርስቲያን ተግባር እንደሆነ የተፈጥሮ እዉቀት እንኳን ይነግራችኋል እናምእነርሱ በዛ መልክ ካጠመቁ ስለዚህ የማጥመቂያ መንገዱ እሱ ነዉ ማለት ነዉ ይሄ ጠንከር ያለ ነዉ ብላችሁ ካሰባችሁ ማንኛዉም በጌታኢየሱስ ክርስቶስ ስም ያልተጠመቀ ሁሉ ዳግም መጠመቅ አለበት ስለሚለዉ ጉዳይስ ምን ታስባላችሁ?

የሐዋር ስራ 19፡1-6"አጵሎስም በቆሮንጦስ ሳለ ጳዉሎስ በላይኛዉ አገር አልፎ ወደ ኤፌሶን መጣ አንዳንድ ደቀመዛሙርትንም አገኘባመናችሁ ጊዜ መንፈስቅዱስን ተቀበላችሁን አላቸዉእነርሱም አልተቀበልንም መንፈስ ቅዱስ እንዳለ ስንኳ አልሰማንም አሉት እንኪያበምን ተጠመቃችሁ አላቸዉ እነርሱም በዮሐንስ ጥምቀት አሉት ጳዉሎስም ዮሐንስስ ከእርሱ በኋላ በሚመጣዉ በኢየሱስ ክርስቶስ ያምኑዘንድ ለሕዝብ እየተናገረ በንስሐ ጥምቀት አጠመቀ አላቸዉ ይህንም በሰሙ ጊዜ በጌታ በኢየሱስ ስም ተጠመቁ ጳዉሎስም እጁንበጫነባቸዉ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ወረደባቸዉ በልሳኖቸም ተናገሩ፡፡ ሰዎቹም ሁሉ አሥራ ሁለት ያህሉ ነበር፡፡"ይሄዉ እዚጋ እነዚህ በኤፌሶን ያሉ መልካም ሰዎችስለሚመጣዉ መሲህ ሰምተዉ ነበር በንስሃ ጥምቀትም ወደፊት የሚመጣዉን ኢየሱስን ተመልክተዉ ተጠምቀዉ ነበር አሁን ግን ወደኃላወደ ኢየሱስ ተመልክተዉ ለሀጥያት ስርየት መጠመቅ አለባቸዉ፡፡ መንፈስ ቅዱስን የመቀበያ ጊዜ ነዉ ልክ በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስስም ሲጠመቁ ጳዉሎስ እጁን ጫነባቸዉ እናም መንፈስ ቅዱስ በላያቸዉ ላይ ወረደ፡፡

ዉድ ወዳጆቼ ሆይ በኤፌሶን እንዳሉት ሰዎች መልካምሰዎች ደህንነታቸዉ የተጠበቀ እንደሆነ እንደተሰማቸዉ የሚሰማችሁ ሰዎች ካላችሁ ምን ያህል እርቀት ተጉዘዉ እንደመጡ አስተዉሉየሚመጣዉን መሲህ እስከመቀበል ደርሰዉ ነበር እርሱን ለማግኘት ዝግጁ ነበሩ ነገር ግን እነዚህ ሰዎች እሱን አለማግኘታቸዉ ብቻሳይሆን መጥቶ ዳግም ተመልሶ ሄዷል በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ስም መጠመቅ ያስፈልጋቸዉ ነበር በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ያስፈልጋቸዉነበር፡፡

በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስስም ከተጠመቃችሁ እግዚአብሔር በመንፈሱ ይሞላችኋል ይህ ቃሉ ነዉ፡፡ ቀደም ሲል ያነበብነዉ ሐዋ ስራ 19፡6 የሐዋ ስራ 2፡38ቃል ፍጻሜ ነዉ

> *"ንስሃ ግቡ ሃጥያታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁየመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ፡፡"*

ተመልከቱ ጳዉሎስ በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ ጴጥሮስ በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ የተናገረዉን እራሱን ተናገረየተነገረዉ ቃል ደግሞ አይቀየርም፡፡ ከባለሀምሳ ቀን አንስቶ የመጨረሻዉ የተመረጡ ሁሉ እስኪጠመቁ ድረስ ተመሳሳይ መሆን አለበትገላቲያ 1፡8

> *"ነገር ግን እኛ ብንሆን ወይም ከሰማይ መልአክ ከሰበክንላችሁ ወንጌል የሚለይ ወንጌልን ቢሰብክላችሁየተረገመ ይሁን፡፡"*

አሁን አንዳንድ ኢየሱስብቻ የምትሉ ሰዎች አጠማመቃችሁ ስህተት ነዉ፡፡ የምታጠምቁት በጠለቀ ዉኃ ዉስጥ መጠመቅ ብቻ እንደሚያድን አድርጋችሁ ሰዎችንለመዳን ነዉ የምታጠምቁት መዳን በዉሃ ጥምቀት አይገኝም የመንፈስ ቅዱስ ስራ ነዉ፡፡ በመንፈስ ተመርቶ ትእዛዙን ያስተላለፈዉሰዉ እንዲህ ብሎ ነዉ "ንስሃ ግቡ እናም በጌታ ኢየሱስ ስም ተጠመቁ" እዚህ ላይ ዉሃዉ ያድናልአላለም ያለዉ ተግባሩ "ለእግዚአብሔር የበጎ ሕሊና ልመና ነዉ፡፡"ይሄዉ ነዉ፡፡

1ኛ ጴጥሮስ 3፡21

> *"ይህም ዉኃ ደግሞ ማለት ጥምቀት ምሳሌዉ ሆኖ አሁንያድነናል የሰዉነትን እድፍ ማስወገድ አይደለም ለእግዚአብሔር የበጎ ሕሊና ልመና ነዉ እንጂ ይህም በኢየሱስ ክርስቶስ ትንሳኤነዉ፡፡"*

እኔ አምነዋለሁ፡፡

ታርክ በጌታ ኢየሱስክርስቶስ ስም ዉጪ ጥምቀት እንዳለ ያረጋግጣል የሚል የተሳሳተ ሐሳብ ያለዉ ሰዉ ካለ እራሳችሁ ታሪኩን አንብባችሁ እንድታረጋግጡምክር እሰጣለሁ፡፡ ቀጣዩ ታሪክ በሮም ሀገር ኢየሱስ ከሞተ ከ 100 አመታት በኃላ ታየም ተብሎ በሚታወቅመጽሄት ላይ የተመዘገበ እዉነተኛ የሆነ የጥምቀት ድርጊት ነዉ እ.አ.አ ዴሴምበር5 1955 ዓ.ም "ዲያቆኑ እጁን ወደላይ አነሳ እና ፓብሊዩስ ዲሲዩስ ወደ ማጥመቂያ በር ዘለቀ በማጥመቂያ ገንዳ ዉስጥ እስከ ወገቡድረስ ጠልቆ የቆመዉ እንጨት ሻጩ ማርከስ ቫስካ ነበር ፓብሊዩስ በማጥመቂያ ገንዳ ዉስጥ ከአጠገቡ መጥቶ ሲቆም ፈገግ እያለነበር፡፡ ክሪድስ ብሎ ጠየቀ ክሪዶም ለፓብሊዩስ እንዲህ ብሎ መለሰለት በጲላጦስ ግዛት ስር ለመስቀል ሞት ታልፎ በተሰጠዉበኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ መዳኔ እንደሚገኝ አምናለሁ የዘላለም ህይወት አገኝ ዘንድ ከእርሱ ጋር አብሬ ሞቻለሁ ካለ በኃላ ወደኃላ እራሱን ወደ ዉሃ ሊያስገባ ሲል ጠንካራ ክንድ ሲደግፈዉ ተሰማዉ ከዛም ወደ ቀዝቃዛ ዉሃ ዉስጥ እየሸፈነዉ በጌታ ኢየሱስ ስም አጥምቅሃለሁ" የሚል የማርከስ ድምጽ ተሰማ፡፡

እዉነታዉ እስከጠፋበት ጊዜ ድረስ(እዉነቱእስከተመለሰበት አሁን እስካለንበት ዘመን ማለትም ከኒቂያ ጉባኤ አሁን እስካለንበት ዘመን ድረስ) ጥምቀት ይከናወን የነበረዉበጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ነበር፡፡ አሁን ግን ተመልሶ መጥቷል መንፈስ መገለጥን ሊሰጥ ሲፈልግ ሴይጣን መገለጡን ሊያስቆምአይችልም፡፡

አዎ ሶስት አምላክ ቢኖርኖሮ በአባት፤በልጅ እና በመንፈስ ቅዱስ ስም ማጥመቁ መልካም ይሆን ነበር ነገር ግን ለዮሐንስ የተሰጠዉ መገለጥ አንድ አምላክእንዳለ ብቻ ነዉ ስሙም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ነዉ እምናጠምቀዉም አንድ እና አንድ በሆነዉ አምላክ ብቻ ነዉ፡፡

ለዛም ነዉ ጴጥሮስ በባለሐምሳ ቀን ባጠመቀበት መልኩ ያጠመቀዉ ለተሰጠዉ መገለጥ እዉነተኛ እና ታማኝ መሆንነበረበት “በርግጥ የእስራኤል ወገን ሁሉ እግዚአብሔር እናንተ የሰቀላችሁትን ኢየሱስን ጌታም ክርስቶስም እንዳደረገዉይህን ይወቅ፡፡” ይሄዉ እዚህ ጋር “ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ”

ኢየሱስ ሁለቱንም ጌታ እናክርስቶስ ከሆነ ስለዚህ እርሱ(ኢየሱስ) እራሱ አባት፤ልጅ እናመንፈስ ቅዱስ ነዉ እንጂ ሌላ ሊኖር አይችልም በአንድ አካል በስጋተገለጠ እንጂ በሶስት አካል ዉስጥ ያለ አንድ አምላክ አይደለም የስላሴ አማኞችን እግዚአብሔር ይባርካቸዉ ነገር ግን አንድአምላክ አንድ አካል በሶስት ታላላቅ መገለጫዎች እና ስያሜዎች የተገለጠ ነዉ፡፡ ጌታ(አብ) እና ክርስቶስ(መንፈስ ቅዱስ)ኢየሱስ ነዉ ምክንያቱም እርሱ (ኢየሱስ) ሁለቱንም ስለሆነ (ጌታም ክርስቶስም)

ይሄ የሙላተ መለኮትን እዉነተኛ መገለጥ ሊያሳየንካልቻለ ሌላ ሊያሳየን የሚችል ነገር የለም፡፡ ጌታ ማለት ሌላ አይደለም ክርስቶስ ማለት ሌላ ማለት አይደለም ይሄ ኢየሱስ እራሱነዉ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ - አንድ አምላክ፡፡

ፊሊጶስ አንድ ቀን ለኢየሱስ እንዲህ አለዉ “ጌታ ሆይ አብን አሳየን እናይበቃናል ኢየሱስ መልሶ ይሄንያህል ጊዜ ከእናንተ ጋር ስሆን አታዉቀኝምን እኔን ያየ አብን አየ ስለምን አብን አሳየን ትላለህ እኔ እና አብ አንድ ነን፡፡”

አንድ ጊዜ ለአንዲት ሴት ይሄን ጥቅስ ጠቅሼላታለሁ እንዲህ አለችኝ “ቆይ ቆይ አንድ ጊዜ ወንድምብራንሃም አንተ እና ባለቤትህ አንድ ናችሁ አይደል”

“በዛ መልኩ አይደለም ”አልኳት“

እሷም እንዲህ አለችኝ “ይቅርታ አድርግልኝ?”

እኔም እንዲህ አልኳት“እኔን ታይኛለሽ?”

እሷም መለሰችልኝ “አዎ”

እኔም አልኳት“ባለቤቴንስ ታያታለሽ?”

እሷም መለሰች “አላያትም”

እኔም አልኳት “ስለዚህ ኢየሱስ እኔን ያየ አብን አይቷል ያለበት አንድነት ከዚህ የተለየ ነዉ፡፡”

ነብዩ ሲጨልም ብርሃን ይሆናል አለ በመንፈሳዊ የመዝሙር መጽሀፍ ላይ እንዲህ ተጽፏል

በጨለማዉ ብርሃን ይሆናል

የክብርን መንገድ በርግጥ ታገኘዋለህ

የዉሃዉ መንገድ የዛሬ ብርሃን ነዉ

በዉዱ በኢየሱስ ስም የተቀበረ

ወጣቱም አዛዉንቱም ከሃጥያታችሁ ንስሃ ግቡ

መንፈስ ቅዱስ በርግጥ ይገባል

የጨለማዉ ብርሃን መጥቷል

እግዚአብሔር ና ክርስቶስ በርግጥ አንድ ናቸዉ

ብዙም እሩቅ አልነበረም ከአይሁዳዊ መምህር ጋር ሳወራእንዲህ አለኝ “እናንተ አህዛቦች ለአንድ አይሁዳዊ እግዚአብሔርን ለሶስት ለያይታችሁ ልትሰጡት አትችሉም ከዛ በተሻለእናዉቃለን፡፡”

እኔም እንዲህ አልኩት “ልክ ነህ መምህር ሆይ እግዚአብሔርን ለሶስት አንከፋፍለዉም በነብያቶች ታምናለህ አይደል?”

እሱም እንዲህ አለ “በርግጥ አምናለሁ”

“ኢሳያስ 9፡6 ላይ ያለዉንስ ታምናለህ?”

“አዎ”

ይናገርለት የነበረዉ ነብይ ማን ነበር?

“መሲሁ ነዉ”

መሲሁ ከእግዚአብሔር ጋር ያለዉ ግንኙነት ምንድን ነዉ? አልኩት

እሱም መለሰልኝ “እርሱ እራሱ እግዚአብሔር ነዉ”

እኔም መለስኩለት “እዉነት ነዉ ትክክል ነዉ አሜን፡፡”

እግዚአብሔርን በሶስት አካል ወይም በሶስት ክፍል ልናስቀምጥ አንችልም፡፡ ለአንድ አይሁዳዊአባት ልጅ እና መንፈስ ቅዱስ ብለህ ልትነግረዉ አትችልም ይሄ ሀሳብ ከየት እንደመጣ በፍጥነት ይነግርሃል አይሁዶች ይሄ እምነትየተመሰረተዉ በኒቂያ ጉባዔ ላይ እንደሆነ ያዉቁታል፡፡ ልክ እንደ አረመኔ አድርገዉ ቢንቁንም አያስደንቅም፡፡

ስለማይቀየረዉ አምላክ አወራን ይሄን አይሁዶችምያምኑታል፡፡ ነገር ግን ቤተክርስቲያን የማይለወጠዉን አምላክ ከአንድ ወደ ሶስት ለወጠችዉ ሆኖም ግን በጨላማዉ ሰአት ብርሃኑተመልሷል እንዴት ያለ የሚደንቅ ነገር ነዉ ይሄ እዉነት እስራኤላዊያን ወደ ፓልስቲን በተመለሱበት ወቅት መምጣቱ እግዚአብሔርእና ክርስቶስ አንድ ነዉ ይሄ ኢየሱስ ጌታም ክርስቶስም ነዉ፡፡

ዮሐንስ መገለጥ ነበረዉመገለጡም ኢየሱስ ነበር እራሱንም በመጽሃፍ ቅዱስ እንዲህ ብሎ ገለጸዉ - “እኔ ያለ፤የነበረ፤የሚመጣ እኔ ነኝ ሁሉን ቻይ አሜን”

መገለጡ ከእናንተ በላይ ከሆነባችሁ ወደ ላይ ቀና ብላችሁ እግዚአብሔርን ተመልከቱት ማግኘት የምትችሉበትብቸኛ መንገድ ይሄ ነዉ፡፡ መገለጥ ከእግዚአብሔር ብቻ ይመጣል በሰዉ በኩል፤ በተፈጥሮ በኩል ሳይሆን በመንፈሳዊ መገኘት ብቻይመጣል፡፡ መጽሀፍቅዱስን አስሬ ብታሰላስሉት ያ መልካም ቢሆንም እንካን ያም ግን አይሰራም ከእግዚአብሔር ብቻ የሚመጣ መገለጥመሆን አለበት በቃሉ ላይ እንዲህ ይላል በመንፈስ ካልሆነ በቀር ሰዉ ኢየሱስ ክርስቶስ ነዉ ሊል አይችልም መንፈስ ቅዱስናመንፈስቅዱስ ብቻ ነዉ ኢየሱስ ክርስቶስ የተቀባዉ አምላክ ነዉ እንድትሉ መገለጥን የሚሰጣችሁ፡፡

የእግዚአብሔር መንፈስሊገልጠለት ካልወደደ ወይም ሊያድነዉ ካልወደደ በቀር የእግዚአብሔርን ነገር ሊያዉቅ የሚችል ሰዉ የለም፡፡ በአለም ላይ ካለዉከምንም ነገር በላይ መገለጥን ይሰጠን ዘንድ እግዚአብሔርን ልንጠራዉ ያስፈልጋል፡፡ መጽሀፍ ቅዱስን ተቀብለናል በዉስጡ ያለዉንምታላቅ እዉነት ተቀብለናል ነገር ግን የመንፈስ ቅዱስ መገለጥ ባለመኖሩ የተነሳ ለብዙ ሰዎች እዉነት አይመስላቸዉም ቃሉአላነቃቃቸዉም፡፡

መጽሃፍ ቅዱስ በ2ኛ ቆሮንጦስ 5፡21 ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ባለን ህብረት የእግዚአብሔርጽድቆች እንደሆንን ይናገራል፡፡ አገኛችሁት በክርስቶስ በመሆናችን በራሱ በእግዚአብሔር ጻድቀናል ይላል እርሱ(ኢየሱስ) ስለእኛሐጥያት ሆነ፡፡ ሀጥያተኛ ሆነ አይልም፡፡ ከእርሱ ጋር በሚኖረን ህብረት የእግዚአብሔር ጻድቃን እንሆን ዘንድ ለእኛ ሀጥያት ሆነነዉ የሚለዉ፡፡

እዉነታዉን እንቀበል ካልን (የግድም መቀበል አለብን)በእኛ ምትክ ፋንታ ቀጥታ ሀጥያት እንደሆነ ስለዚህ ከእርሱ ጋር ባለን ህብረት ደግሞ የእግዚአብሔር ጻድቃን የመሆናችንን እዉነታመቀበል ይገባናል፡፡ አንዱን አለመቀበል ሌላኛዉን አለመቀበል ነዉ አንደኛዉን መቀበልም ሌላኛዉን መቀበል ነዉ፡፡ መጽሃፍ ቅዱስእንዲህ እንደሚል እናዉቃለን፡፡ ሊካድ የሚችል አይደለም፡፡

ስለዚ ጉዳይ ያለዉ መገለጥ ግን ተዘንግቷል ለብዙሃኑ የእግዚአብሔር ልጆችም በመጽሐፍ ቅዱስ ዉስጥ ያለአንድ ጥሩ ጥቅስ ሆኖ ይታሰባል እንጂ የምር እዉነታ እንደሆነ አይታሰበም በህይወታችን ህያዉ እንዲሆን ማድረግ አለብን፡፡ ይህምደግሞ መገለጥ ያስፈልገዋል፡፡

ሁለት ሊያስደንቃችሁ እናሊረዳችሁ የሚችል ነገር ልንገራችሁ አዲስ ኪዳን መጀመሪያ የተጻፈዉ በግሪክ ቋንቋ እንደሆነ የማያምን ተማሪ አለ፡፡ ሁሉምየመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች ወንጌልን ለማዳረስ ሲባል አስተዋጽኦ ሊያበረክቱ የሚችሉ ሶስት ሀገራትን እግዚአብሔር ሰጥቷል ይላሉ፡፡ አለምአቀፍ የሆነ ቋንቋ የሰጣቸዉ ግሪኮች እዉነተኛ እምነት እና በአዳኙ በኩል የሚገኝ የእግዚአብሔር እዉቀትን የሰጣቸዉአይሁዶችን ሰጠን እንዲሁም በህጎችና በአዉራ ጎዳና ስርአቶች ጠንካራ የተገነባ የኑገሰ ነገሰት አገዛዝ ያላትን ሮም ሰጠን፡፡ስለሆነም እዉነተኛ እምነት አለን፤ለብዙ ሰዎች ያንን እምነት የምንገልጽበት ቋንቋ አለን በሚታይ መልኩ እምነቱንም በአካልልናዳርስ የቻልንበት መንግስትና መንገድ አለን፡፡ ታሪክን መሰረት አድርገን ከተናገርን ደግሞ ትክክለኛ ነገርይመስላል፡፡

ዛሬ ላይ የግሪክ ምሁራን እንዲህ ይላሉ የግሪክ ቋንቋ መጽሐፍ ቅዱስ በተጻፈበት ዘመንፍጹምና ትክክለኛ ነበር አንድ ተማሪ በደንብ የሚያጣራ እና ሰዋሰዋዊ ይዘቱን ጠብቆ የሚያጠናዉ ከሆነ በርግጥም የአዲስ ኪዳንመጽሃፍ ምን እንደሚያስተምር በደንብ ማወቅ ይችላል፡፡ ነገር ግን ይሄ ነገርዝምቦሎ ሀሳብ ብቻ ነዉን? እዉነታኛ ነገር አይደለምን? የትኛዉም የግሪክ ምሁራኖች ከአንድ ተቋም ከሌላኛዉ ተቋም እንደሚከራከሩ አይታወቅምን? የአንድ ተቋም ተማሪዎችከሌላኛዉ ተቋም ተማሪዎች የሚከራከሩ አይደሉምን? ደግሞም የሚከራከሩት ተመሳሳይ በሆነዉ በዛዉ የግሪክ የሰዋሰዉ ህግን መሰረት አድርገዉአይደለምን? በርግጥም እንደዚሁ ነዉ፡፡

ወደ ኋላ ተመልሰን በጴርጋሞን ዘመን በ325 አመት ከኒቂያዉ ጉባኤ አስቀድሞ አርዩስ እናአትናስዩስ የተባሉ ታላቅ አጥኚዎች የግሪክ ቃላትን መሰረት አድርገዉ ታላቅ የአስተምህሮት ዉጊያ አላደረጉምን?በጣም በጋለ ስሜት እናአለምአቀፍ በሆነ ክርክር፡፡ ያ የታሪክ አጥኚዉ አለም በሁለትአናባቢ ድምጾች ተከፋፈለች ብሎ አልተናገረም፡፡

አሁን ግሪክኛ ፍጹም ከሆነ እና ከእግዚአብሔር የተወሰነ ከሆነ ለምንድነዉ ይሄን ያህልአለመግባባቶች የሆኑት? በርግጥም እግዚአብሔር ግሪክኛን ማወቅ አለባችሁ አላለም ዛሪ ላይ ግን ስለ ግሪክ አለመግባባቶች ተፈጥረዋልበደ/ር መሲ ክሮሳን የተጻፈዉን “ኤክስ ሬይ የተነሳዉ የክርስቶስ ፓራላይዝድ ቤተ ክርስቲያን” የተሰኘዉን መጽሃፍ እንደምሳሌ ብንወስድ በዛ መጽሃፍ ዉስጥ ብዙ የታደሱየግሪክ ሰዋሰዎችን ጠቅሶ ለራሱ እርካታ የማይለዋወጡት የግሪክ ሰዋሰዋዊ ቋንቋዎች መጽሃፍ ቅዱስ ላይ ከዳግም ዉልደት አስከትሎሰዉ በመንፈስቅድስ እንደሚጠመቅ ያረጋግጣሉ ብሏል ግልጽ በሆነምሁኔታ ሴት መድረክ ላይ መናገር እንደምትችል እና የቃል ትንቢት ማለት ስብከት ነዉ ብሏል ነገር ግን የሱን ያክል ብቃት ያላቸዉየግሪክ አጥኚዎችን ሊያሳምናቸዉ ችሏል? ፈጽሞ አልቻለም፡፡ እናንተ ማድረግ የሚጠብቅባችሁ ነገር እነዚህ አጥኚዎች የተቃወሙበትንምልከታ ማንበብ እና ጥቅሶቻቸዉን መስማት ብቻ ነዉ፡፡

አሁን እኔ ያልኩት ብቻአይደለም እዉነቱ ትንሽ ከዚህም ባሻገር እንሂድ ዛሬ ላይ መጽሃፍ ቅዱስ መጀመሪያ የተጻፈዉ በምድር ላይ ኢየሱስ በነበረበት ጊዜበተጠቀመዉ የ አረማይክ ቋንቋ ነዉ የሚሉ አሉ የእነዚህ አመለካከትም መነሻ ሀሳብ በተለምዶ ሊባል እንደሚችለዉ ሰዎቹ በግሪክኛየሚናገሩም የሚጽፉም ስላልሆኑ የሚል ነዉ፡፡ እናም ብቻ እዉነታዉታሪክ አጥኚዎቻችን እርስ በእርሳቸዉ ተከፋፍለዋል፡፡

ለምሳሌ ያህል ጎበዝ አጥኚ የሆነዉ ዶ/ር ስኮንፊልድ ራሱን ደስ ለማሰኘት ያህል ባደረገዉጥናት የአዲስ ኪዳን መጽሀፍ የተጻፈዉ በዛን ጊዜ

የነበሩ የግሪክ ሰዎች በሚናገሩት ቋንቋ ነዉ የሚል ማረጋገጫ አቅርቧል፡፡ ለማረጋገጫነትም የሚሆኑትን ልዩ ል ጥናታዊ ሰነዶች አደራጅቶ አቅርቧል፡

ነገር ግን በሌላ መንገድ ደግሞ ዝነኛ ተመራማሪ የሆነዉ ዶ/ር ላምሳ አለ የአዲሲ ኪዳን መጽሐፍ የተጻፈዉበአረማይክ ቋንቋ ነዉ ብሎ የሚያምን እና የእሱንም ሀሳብ የሚጋራዉ ጎበዝ የታሪክ አዋቂ የሆነዉ ቶይንቢ የተባለዉ ሰዉ የሰዎቹቋንቋ የነበረዉ ግሪክ ሳይሆን አረማይክ እንደሆነ የሚደግፍ ሰዉአለ፡፡ ስለዚህ አዲስ ኪዳን የተጻፈዉ በአረማይክ ሊሆን ይችላል ይላሉ፡፡

ሆኖም ግን ስለዚህ ጉዳይብዙ ትኩረት ከመስጠታችን በፊት የኪንግ ጀምስ መጽሃፍን እና የዶ/ር ላምሳን ትርጉም ሁለቱንም እናንብባቸዉ፡፡ ለእኛ ደስታብሁለቱም በኩል በሚያስደንቅ ሁኔታ ምንም አይነት የይዘት ወይም የአስተምህሮት ልዩነት በሌለዉ መልኩ ተመሳሳይ ናቸዉ፡፡

ምናልባትም እነዚህ በቅርቡ የተገኙት በእጅ የተጻፉ ጽሁፎች እና በቅርቡ የታተሙ ህትመቶች ቀድሞምከምናዉቀዉ ጋር ተመሳሳይ እንደሆኑ ማረጋገጫ ይሆኑ ዘንድ እንዲታወቅ እግዚአብሔር ፈቅዶ ነዉ ብለን ልንደመድም እንችላለን፡፡

የመጽሀፍ ቅዱስ አጥኚዎችመጽሐፍ ቅዱስ ስለተጻፈበት ቋንቋ ላይ ባላቸዉ የጠለቀ እዉቀት ላይ ተመስርቶ እንደማይተረጎም አሁን ማየት ትችላላችሁ፡፡ አሁንምግን አስተሳሰባችሁ በባህል ተጋርዶ ይሄን ማየት ካልቻላችሁ ሌላ አንድ ተጨማሪ ምሳሌ ልስጣችሁ

ፈሪሳዊያን እና ሰዱቃዊያን በ33 ዓ.ም ላይ የብሉይ ኪዳን መጽሃፍ የተጻፈበትን ትክክለኛ ሰዋሰዉ እናትክክለኛ የቃሉ ትርጉም በደንብ ያዉቁ እንደነበር የሚጠራጠር ማንም የለም ነገር ግን የተለቀ እዉቀት ኖሯቸዉ እንኳን በልጁየተገለጠዉን የእግዚአብሔር የተሰፋ ቃል አመለጣቸዉ፡፡

ከዘፍጥረት እስከ ሚልኪያስባሉት መጻህፍት ምእራፎች ሁሉ ስለእሱ እና ስለ አገልግሎቱተቀምጧል ሆኖም ግን በመንፈስ ከበራላቸዉ ከጥቂቶች በቀር ሁሉም ሊያዉቁት አልቻሉም አመለጣቸዉ፡፡

አሁን ወደ ድምዳሜ መድረስእንችላለንበቃሉ ዉስጥ እንደምናገኘዉ የፈለገዉን ያህል የቀደምት እና ምርጥ የእጅ ጽሁፎችን ስለ ቃሉ የተጻፉትን የቻልነዉን ያህል ብንፈልግም በማጥናት እና ጥቅሶችን በማመሳከር የፈለገትሁታኖች ብንሆን እዉነተኛ ትርጉሙን ልናገኝ አንችልም፡፡

ትክክለኛዉን ነገር ለማግኘት ከእግዚአብሔር ዘንድ መገለጥ ያስፈልጋል ጳዉሎስም በትክክል የተናገረዉ ይህንነዉ "መንፈሳዊዉን ነገር ከመንፈሳዊዉ ነገር ጋር አስተያይተንመንፈስ በሚያስተምረን ቃል ይህን ደግሞ እንናገራለን እንጂ የሰዉ ጥበብ በሚያስተምረን ቃል አይደለም፡፡"1ኛቆሮ 2፡12 እዉነተኛ መገለጥ እግዚአብሔር እራሱየራሱን ቃል የተነገረዉን ተስፋ ቃል በተግባር በማሳየት የሚያረጋግጥ ሲሆን ብቻ ነዉ፡፡

አሁን ማንም ሰዉ በተናገርኩት ነገር በተሳሳተ መንገድእንዳይተረጉመዉ መጽሐፍ ቅዱስ ትክክለኛ እና እዉነተኛ እንደሆነ ሙሉ በሙሉ አምናለሁ ኢየሱስ ምድር ላይ በነበረ ጊዜ የብሉይኪዳን መጽሃፍን ሙሉ በሙሉ ትክክል እንደሆነ አረጋግጦታል የእኛም የአዲስኪዳኑ መጽሀፍ በተመሳሳይ መልኩ የተቀናበረ ነዉ፡፡በዚህ ጉዳይ ላይ አትሳሳቱ የማይለዋወጠዉ የእግዚአብሔር ቃል ዛሬም አለን ማንም ሰዉ ደግሞ ሊቀንሰዉም ሆነ ሊጨምርበትአይችልም፡፡ነገር ግን ያንን ቃል የሰጠዉ ያዉ መንፈስ ደግሞ ያስተምረን ዘንድ ለኛም ያስፈልገናል፡፡

አ፡ የመንፈስ መገለጥ ምን ያህል ያስፈልገናል አዲስመጽሐፍ ቅዱስ አያስፈልገንም አዲስ ትርጉምም አያስፈልገንም ምንም እንካን አንዳንዶቹ መልካም ቢሆኑም እነሱንም አልቃወምም ነገርግን የመንፈሱ መገለጥ ያስፈልገናል፡፡ እናም እግዚአብሔር ይመስገን ቃሉን በመንፈሱ አማካኝነት ሊገልጥልን ስለሚፈልግየፈለግነዉን ማግኘት እንችላለን፡፡

እግዚአብሔር ቀጣይነት ያለዉና አሸናፊ የሆነ መገለጥንበመንፈሱ አማካኝነት ይጀምር አ፡ ቤተክርስቲያን ትኩስ የሆነ መገለጥ ካገኘች ብቻ ነዉ ህያዉ የሆነዉ ቃል የሚገለጥባት ታላላቅስራዎችን እናደርጋለን በሰማያት ያለዉን አባታችንንም ማክበር እንችላለን፡፡

## ከሀጥያት ነጻ መዉጣት

ራዕይ 1፡5

*"ለወደደን ከሀጥያታችንም በደሙ ሳጠበን""ማጠብ" የሚለዉ ቃል "አሳቀቀን"*

ማለት ነዉ "በገዛ ደሙ ከሀጥያታችንላቀቀን"እጅግ አያስደንቅም?ነገር ግን በመንፈስእያያችሁት ነዉ? ሀሳቡን አገኛችሁት? ሙሉ በሙሉ ከገዛ ሀጥያታችን ያላቀቀን በገዛ ደሙነዉ፡፡ የእግዚአብሔር ደም ነዉ፡፡

ጴጥሮስ የክርስቶስ ደም አለዉ፡፡ ጳዉሎስ የጌታ ደም አለዉ፡፡ የሶስት አካላት አይደለም የአንድ አካልነዉ፡፡ ይሄዉ ያ መገለጥ ተመልሶ መጣ አንድ አምላክ፡፡ ያ ሁሉን የሚችለዉ ያህዌ ከድንግል ዉልደት አማካኝነት ለራሱ አካልአዘጋጅቶ በዛ ዉስጥ አደረ ነጻ የሚያወጣን የአምላክ ደም ይባል ዘንድ (ሙሉ በሙሉ ከሀጥያት ነጻ የሚያወጣን) በፊቱም በታላቅደስታ ጠባሳ የሌለብን ሆነን እንታይ ዘንድ፡፡

የብሉይ ኪዳንን ተምሳሌትትፈልጋላችሁ? እስኪ ወደ ዘፍጥረት እንመለስ የመጀመሪያዉ አዳም በሀጥያት ሲጠፋ የመጣልን የከበረ ዜናመልአክ ተላከ ነበር? ሌላ ልጅ? እኛን የመሰለ ሌላ ሰዉ ነበር የተላከዉ? አይደለም ያ የጠፋ ልጅንለመቤዠት እራሱ አምላክ ነበር የመጣዉ ሀሌሉያ! እግዚአብሔር የማዳን እቅዱን ለማንም አምኖ አይሰጥም እራሱን ብቻ ነዉየሚተማመነዉ፡፡

አምላክ ስጋን ለብሶ በመካከላችን አደረ ከራሱም ጋር አስታረቀን ተቤዠን የዳንነዉ በአምላክደም ነዉ፡፡ ዘላለማዊ አምላክ ሀጥያትን ለማስወገድ በፈራሽ ስጋ ዉስጥ አደረ፡፡ ደም ለማፍሰስ እንደ በግ ሆኖ መጣ በደሙምሸፈነን

ይህን አስተዉሉ ያ የእራሱ የአምላክ ደም ስለሆነ ፍጹም ደም ነዉ እናምከቆሻሻችን እና ከሀጥያት እስራትና ሀይል የሚያላቅቀዉ ደግሞ ፍጹም የሆነ ደም ከሆነ ከሀጥያት መላቀቃችንም ፍጹም እና የተሟላነዉ ማለት ነዉ፡፡

*ስለዚህ አሁን ኩነኔ የለም የእግዚአብሔርን ምርጦች ማንይኮንናቸዋል? ያጸደቀን እግዚአብሔር ነዉ (ጻድቃን ብሎ ያወጀዉ) ማን ይኮንነናል? የሞተልን ክርስቶስ ነዉ..."*

ሮሜ8፡33-34 ይሄዉ እዚጋ ሞቱ ደሙን ሰጠን ደሙ ነጻ አወጣን አሁንኩነኔ የለም እንዴትስ ሊኖር ይችላል? ልንኮነን የምንችልበት አንዳች ነገር የለም ምክንያቱም ደሙ ከሀጥያት አላቆናል ነጻወጥተናል ኩነኔ የለብንም ሰዉን አትስሙ ቃሉን ስሙት በደሙ ነጻ ወጥታችኋል፡፡

አሁን በተለያዩ ተቋማቶች ባህልና በዶግማ እንዳትታሰሩ በገዛ ደሙ ነጻ ዉጡ፡፡ አሁንምድረስ እምነታችሁን በስርአቶች ላይ እና በተቋማቶች ላይ ካደረጋችሁ ይሄ በቃሉ ላይ ያላችሁን እምነት እንዳጣችሁ ማረጋገጫ ነዉ፡፡

## ነገስታት እና ካህናቶች

ራዕይ1፡6

*“መንግስትም ለአምላኩና ለአባቱም ካህናት እንድንሆን ላደረገ ለእርሱ ከዘላለም እስከዘላለም ድረስ ክብርናሀይል ይሁን አሜን፡፡”*

“አደረገን!”በደንብ ትኩረት ልንሰጣቸዉየሚገቡ አንዳንድ እዉነታዎች አሉ ይሄ አንዱ ነዉ እርሱ! እርሱ አደረገን! ማዳን የእርሱ ስራ ነዉ ማዳን የጌታ ነዉ ሁሉ በጸጋየሆነ፡፡ ለአላማ ዋጀን፡፡ ለአላማ ገዛን፡፡ እኛ ነገስታቶች ነን መንፈሳዊ ነገስታቶች በምድር ላይም እርሱ በዙፋኑ ላይበተቀመጠ ጊዜ እኛም አብረን እንነግሳለን ነገር ግን አሁን በመንፈሳዊዉ መንግስት ላይ መንፈሳዊ ነገስታቶች ነን

ሮሜ 5፡17 ላይ እንዲህ ይላል

*“በአንዱም በደል ሞት በአንዱ በኩል ከነገሰ ይልቁን የጸጋን ብዛትና የጽድቅን ስጦታ ብዛትየሚቀበሉ በአንዱ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በሕይወት ይነግሣሉ፡፡”*

እንዲሁም ቆላሲዮስ 1፡13 ላይ

*“እርሱ ከጨለማ ሥልጣንአዳነን ቤዛነቱንም እርሱንም የኃጢአትን ስርየት ወዳገኘንበት ወደ ፍቅሩ ልጅ መንግስት አፈለሰን፡፡”*

አሁን ላይ ከክርስቶስ ጋርየነገስነዉ በሃጥያት ላይ ነዉ በአለም፤ በስጋ ና በዲያብሎስ ላይ ነዉ፡፡ ምስጋና እና ክብሩን እያሳየን በእኛ ዉስጥ ያለዉክርስቶስ እራሱን ደስ የሚያሰኘዉንና የፈቀደዉን ሁሉ እያደረገ፡፡ በአሁን ሰአት ክርስቶስ ኢየሱስ ባለበት በሰማያዊዉ ስፋራ ላይነግሰናል፡፡

“ካህናቶች አደረገን” አዎ የእርሱ ካህናቶች አደረገን የተቀደሱ የከንፈሮቻችንን መንፈሳዊ ምስጋና እንድናቀርብ ህይወታችንን እርሱን ደስየሚያሰኛዉ አድርገን እያቀረብን በእዉነት እና በመንፈስ እንድናመልከዉ፡፡ እየማለድን እና አቤቱታ እያቀረብን የእግዚአብሔርነገስታት እና ካህናት እንድንሆን፡፡ አለም ወደ እኛ ባይቀርብ አያስደንቅም እኛ መልካም ስራዎችን ለማድረግ ሸክም ያለብንየተለየን ሰዎች ስለሆንን፡፡ ልክ እንደ እርሱ የአባታችን ልጆች ለመሆን ዳግም የተፈጠርን ሰዎች ነን፡፡

## የሚመጣዉ ጌታ

ራዕይ 1፡7

*“እነሆ ከደመና ጋር ይመጣል ዓይንም ሁሉ የወጉትም ያዩታል የምድርም ወገኖች ሁሉ ስለ እርሱ ዋይ ዋይ ይላሉአዎን አሜን፡፡”*

እየመጣ ነዉ፡፡ ኢየሱስ እየመጣ ነዉ፡፡ ጌታ እየመጣነዉ፡፡ ነብዩ እየመጣ ነዉ፡፡ ካሕናችን እና ንጉሳችን እየመጣ ነዉ፡፡ ሁሉ በሁሉ የሆነዉ እየመጣ ነዉ፡፡ አዎ ጌታ ኢየሱስ ሆይቶሎ ና አሜን፡፡

እየመጣ ነዉ፡፡ የክብር ደመና ወደ ሰማይ ባረገበትተራራ ላይ እንደታየዉ ልብሱ እስኪያንጸባርቅ ድረስ የእግዚአብሔር ክብር እንደሸፈነዉ ሁሉ በደመና እየመጣ ነዉ፡፡ እናም አይንሁሉ ያየዋል ያ ማለት ይህ ንጥቀቱ አይደለም፡፡ ይሄ ወደ አልም ለመግዛት ዳግም ተመልሶ በሚመጣበት ሰአት የሚሆን ነዉ፡፡ ይሄበተቋማዊ ስርአታቸዉ እና በዶግሞቸዉ ሲወጉት የነበሩ ሁሉ ሲያዩት ዋይ ዋይ የሚሉበት ጊዜ ነዉ ሰዎች ሁሉ ቃል በሆነዉ በእርሱየሚሸበሩበት ጊዜ ነዉ፡፡

ይሄ ከ2500 አመታትበፊት ዘካሪያስ የተነበየዉ የዘካሪያስ የመገለጥ ታሪክ ነዉ ዘካሪያስ 12፡9-14 ሊከናወን ያለ ነገር ነዉ ስሙት

*“በዚያም ቀን በኢየሩሳሌምላይ የሚመጡትን አሕዛብ ሁሉ ለማጥፋት እጋደላለሁ በዳዊትም ቤት ላይ በኢየሩሳሌምም በሚኖሩት ላይ የሞገስንና የልመናን መንፈስአፈስሳለሁ ወደ እርሱም ወደ ወጉት ይመለከታሉ…”*

አሁን ወንጌል ወደኢየሩሳሌም መቼ ነዉ የሚመለሰዉ? የአህዛብ ሙላት ሲፈጸም ነዉ፡፡ ወንጌል ወደ አይሁዳዉያን ሊመለስ ዝግጅት ላይ ነዉ ኦበዚ ዘመን ሊከናወን ያለዉን ነገር ብነግራችሁ ይህ ሊከናወን ያለዉ ታላቅ ነገር ወደ ራዕይ 11 ይወስደናል እናም እነዛ ሁለትምስክሮችን ዉሰዱ እነዛ ሁለቱ ነብያት ሙሴ እና ኤልያስ ወንጌልን ከአህዛብ ወደ አይሁድ ይመልሱታል፡፡ ሁሉ ነገር ተስተካክሎአሁን በዝግጅት ላይ ነዉ፡፡ አይሁዶች መልእክቱን ለአሕዛብ እንዳስተላለፉ አህዛብም ወደ አይሁዶች ይመልሱታል፡፡ ያኔም ንጥቀቱይከናወናል፡፡

አሁን አስታዉሱ ራዕይ እናዘካሪያስን አንብበናል ሁለቱም የሚከናወኑት ከ ታላቁ መከራ በኃላ ነዉ ዳግም የተወለድችዋ የመጀመሪያዋ ቤተክርስቲያን ወደ መከራዉስጥ አትገባም፡፡ ይሄን እናዉቃለን መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረዉ ይሄን ነዉ፡፡

በዛን ቀን ጌታበእየሩሳሌም በሚኖሩት ላይ መንፈሱን እንደሚያፈስስ ይናገራል ለአህዛብ በጊዜያቸዉ የፈሰሰዉ ያ መንፈስ እራሱ ነዉ እናም “ወደ እርሱም ወደ ወጉትይመለከታሉ ሰዉም ለአንድያ ልጁ እንደሚያለቅስ ያለቅሱለታል ሰዉም ለበኩር ልጁ እንደሚያዝን በመራራ ኃዘን ያዝኑለታል፡፡ በዚያቀን በመጊዶን ሜዳ እንደ ነበረዉ እንደ ሐዳድሪሞን ልቅሶ ታላቅ ልቅሶ በኢየሩሳሌም ይሆናል፡፡ ምድሪቱም ታለቅሳለች እያንዳንዱምወገን ለብቻዉ የዳዊት ወገን ለብቻዉ ሴቶቻቸዉም ለብቻቸዉ የናታን ቤት ለብቻዉ ሴቶቻቸዉም ለብቻቸዉ ..”የቀሩት ወገኖች ሁሉእያንዳንዱ ለብቻዉ፡፡

በክብር ደመና ዳግም በሚመለስበት ጊዜ የወጉት አይሁዶች ሁሉ ያዩታል መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ እንደሚል "መቼስ ነዉ የቆሰለህ ሲሉት?""በወዳጆቼ ቤት" ሳለሁ ብሎ ይመልስላቸዋልመስሂ መሆኑ ለተቃወሙት አይሁዶች ብቻ ሳይሆን ከአህዛቦችም መካከል አዳኝ መሆኑን ለተቃወሙ ሁሉ ዋይ ዋይ የሚሉበት ቀንይሆናል፡፡

ልቅሶ እና ጥርስ ማፋጨትይሆናል፡፡ ሞኞቹ ደናግሎች ያለቅሳሉ፡፡ ሞኞቹ ደናግሎች ዘይቱን(የመንፈስ ቅዱስ ተምሳሌት የሆነዉ) ለመቀበል ፈቃደኛ ያልሆኑትንቤተክርስቲያን የሚወክሉ ናቸዉ በብልቃጣቸዉ(የዘይቱ መያዣ አካሉ ተምሳሌት) አስከሚረፍድባቸዉ ድረስ መልካም ሰዎች ሳይሆኑቀርተዉ አይደለም ደናግሎች ነበሩ ይሄ ደግሞ ግብረገብ ስርአት ያላቸዉ መሆኑን አመላካች ነዉ ነገር ግን በብልቃጣቸዉ ዉስጥዘይት አልነበራቸዉም ስለዚህ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ወዳለበት ቦታ ይጣላሉ፡፡

በዘፍጥረት ላይ ባለዉምሳሌ እንዉሰድ ምእራፍ 45 ላይ ዮሴፍ ወንድሞቹን በግብጽ ሲያገኛቸዉ እራሱን እንደገለጠበት ምሳሌ

ዘፍጥረት 45፡1-7

*"ዮሴፍም በእርሱ ዘንድ ቆመዉ ባሉት ሰዎች ሁሉ ፊትሊታገስ አልተቻለዉም ሰዎቹንም ሁሉ ከፊቴ አስወጡልኝ ብሎ ጮኾ ተናገረ ዮሴፍ ለወንድሞቹ ራሱን በገለጠ ጊዜ በእርሱ ዘንድ የቆመማንም አልነበረም፡፡ ቃሉንም ከፍ አድርጎ አለቀሰ የግብጽ ሰዎችም ሰሙ ሰሙ በፈርዖን ቤትም ተሰማ፡፡ ዮሴፍም ለወንድሞቹ እኔዮሴፍ ነኝ አባቴ እስካሁን በህይወት ነዉን? አለ፡፡ ወንድሞቹም ሊመልሱለት ዘንድ አልቻሉም በፊቱ ደንግጠዉ ነበርና፡፡ ዮሴፍምወንድሞቹን ወደ እኔ ቅረቡ አለ ወደ እርሱም ቀረቡ እንዲህም አላቸዉ ወደ ግብጽ የሸጣችሁኝ እኔ ወንድማችሁ ዮሴፍ ነኝ አሁንምወደዚህ ስለሸጣችሁኝ አትዘኑ አትቆርቆሩም እግዚአብሔር ህይወትን ለማዳን ከእናንተ በፊት ሰድዶኛልና፡፡ ይህ ሁለት አመት በምድርላይ ራብ የሆነበት ነዉና የማይታረስበትና የማይታጨድበት አምስት አመት ገና ቀረ፡፡ እግዚአብሔር በምድር ላይ ቅሬታንአስቀርላችሁ ዘንድ በታላቅ መድኃኒትም አድናችሁ ዘንድ ከእናንተ በፊት ላከኝ፡፡ "*

ይህ ቃል ዘካርያስ 12 ላይካለዉ ቃል ጋር በሚያምር መልኩ ስናስተያየዉ ሁለቱን በአንድነት ስናስቀምጣቸዉ ተመሳሳይ ሆኖ እናገኘዋለን ፡፡

ዮሴፍ ወጣት በነበረ ሰዓትበወንድሞቹ ተጠላ ለምንድነዉ በወንድሞቹ የተጠላዉ? ምክንያቱም እርሱ መንፈሳዊ ስለነበረ ነዉ፡፡ ህልምን ስለሚያልምና ስለሚተረጉም አይደለምያ በዉስጡ ያለ ነገር ነዉ ሊያሳይ የሚችለዉ የተሰጠዉን ነገር ነዉ ስለዚህ ወንድሞቹ ሲጠሉት የጠሉት ያለ ምክንያት ነበር እሱግን በአባቱ እጅግ የተወደደ ነበር አባቱ ደግሞ ነብይ ስለሆነ በደንብ ተረድቶታል ይህም የክርስቶስ ፍጹም ተምሳሌትነዉ፡፡

እግዚአብሔር አብ ልጁን ይወደዋል ወንድሞቹ ግን(ጸሃፍትና ሰዱቃዊያን) ጠሉት ምክንያቱም በሽተኞችንስለሚፈዉስ፤ ተአምራቶችን ስለሚያደርግ፤ ትንቢትን ስለሚናገር፤ ራዕዮችን ያይ እና ይተረጉም ስለነበር፡፡ እነዚህ ነገሮችለመጥላት ምክንያት አይሆኑም እነርሱ ግን ጠሉት፡፡ ልክ እንደ ዮሴፍ ወንድሞችም ያለ ምንም ምክንያት እንደጠሉት፡፡

አሁን እነዛ የያቆብ ልጆች ዮሴፍን እንዴት እንዳደረጉት አስታዉሱ ወደ ጉድጓድዉስጥ ወረወሩት፡፡ በብዙ ቀለም ያሸበረቀዉን አባቱ የገዛለትን ልብስ ወስደዉ አባትየዉ በአዉሬ ተብልቶ የሞተ እንዲመስለዉበማሰብ በደም ነክረዉ አመጡት፡፡ ለባርነት ወደ ግብጽ ለወሰዱት ሰዎችም ሸጡት ከዛም በድጋሜ ለአገረ ገዢ ተሸጠ፡፡ የጲጢፋራሚስትም በሀሰት ወደ እስር ቤት እንዲገባ አደረገችዉ ከተወሰኑ ጊዜያት በኃላ ግን እግዚአብሔር የሰጠዉ የነብይነት ስጦታ ወደፈርኦን እንዲሔድ አደረገዉ፡፡ ከዛም ማንም ወደ ፈርኦን መቅረብ የሚፈልግ ሁሉ በየሴፍ በኩል ካልሆነ በቀር መቅረብእስከማይችልበት ድረስ ስልጣን ተሰጠዉ፡፡ ከፈርኦን ቀኝ እንዲቀመጥ ሆኖ ከፍታን አገኘ፡፡

በግብጽ ዉስጥ የነበረዉንየዮሴፍ ህይወት እስኪ እናስተዉለዉ ከክርስቶስ ህይወት ጋር ፍጹም ተመሳሳይ ነዉ፡፡

በአገረ ገዢዉ ቤት በሐሰት ተፈረደበት ያለምክንያትም ተቀጣ ታሰረ ልክ ኢየሱስ ላይእንዳደረጉበት በእስር ቤት ዉስጥ ሆኖ ከእርሱ ጋር ታስረዉ ለነበሩት የወይን ቀጂዉ እና የዳቦ ጋጋሪዉን ህልማቸዉን ተረጎመላቸዉየወይን አሳላፊዉ ወደ ስራዉ ተመለሰ ሌላኛዉ ግን ሞት ተፈረደበት ክርስቶስም በመስቀል ላይ ታሰረ በሰዉና በአምላክ ተፈርዶበትበግራና በቀኙም ሌቦች ከጎኑ ተሰቅለዉ ነበር አንደኛዉ መንፈሳዊ ሞት ሞተ ሌላኛዉ ህይወትን አገኘ እናም አስተዉሉ ኢየሱስከመስቀል ሞት በኃላ በሰማይ ከፍ ከፍ አለ በታላቁ በያህዌ ቀኝ አሁን ተቀምጧል ማንም በእርሱ በኩል ካልሆነ በቀር ወደ አብመቅርብ አይችልም በእግዚአብሔር እና በሰዉ መካከልም አንድ መካከለኛ አማላጅ አለ የሚያስፈልጋችሁም እሱ ብቻ ነዉ፡፡ ሌላ ማርያምወይም ቅዱሳን የሉም ኢየሱስ ብቻ ነዉ ያለዉ፡፡

በዮሴፍ ላይ ያየነዉን ምሳሌ እንዳለ ሆኖ በግብጽ እያለበእያንዳንዱ ባደረገዉ ነገር ሁሉ እየበለጸገ እንደሔደ አስተዉሉ በአገረ ገዥዉ ቤት ሳለ የመጀመሪያ ስራዉ አደገ፡፡ በእስር ቤትእንኳን ሆኖ እድገት አገኘ፡፡ ኢየሱስ ተመልሶ ሲመጣ በረሃዉ እንደ ሮዝ አበባ ይፈነድቃል እርሱ "የባለጸጋ ልጅ ነዉ" በዮሴፍ ዘመን እንደነበረዉ አይነት ብልጽግና እንዳልነበረሁሉ እንደዛ ያለ አለም አይቶት የማያዉቀዉ ብልጽግና ና በረከትበምድር ላይ የሚመጣበት ጊዜ አለ፡፡

እናም አስታዉሱ ዮሴፍ በሚሔድበት ስፍራ ሁሉ መምጣቱንለማሳወቅ መለከት ይነፋል፡፡ ህዝቡ ይጮሃል ለዮሴፍም ይሰግዳሉ ማንም ሰዉ ምንም አይነት ነገር እየሰራ ቢሆን መለከቱ ሲነፋበጉልበቱ ይንበረከካል፡፡ በመንገድ ላይ ሆኖ አንዳች ነገር እየሸጠ እንኳን ሊሆን ይችላል ገንዘብ ለመቀበል ደርሶ ቢሆን እንኳንመለከቱ ሲነፋ ግን የግድ ወደ ታች አጎንብሶ መስገድ አለበት፡፡ የፈለገ ተዋናይም እንኳን ቢሆን ትወናዉን አቋርጦ የዮሴፍመምጣትን የሚያሳዉቀዉ መለከት በተሰማ ሰዓት የግድ ለዮሴፍ ከጉልበቱ ዝቅ ብሎ መስገድ አለበት፡፡ እናም አሁን ባለንበትም ቀናትድንገት የእግዚአብሔር መለከት ሲነፋ ሁሉ ነገር ቀጥ ይላል በክርስቶስ የሞቱ ይነሳሉ ዘላለማዊ ብርሀንን የይዞ ንጋት ይሆናልከዛም ጉልበት ሁሉ ይንበረከካል፡፡ መጽሐፍ እንደሚል በፊሊጶስ 2፡9-11

*"በዚህም ምክንያት ደግሞእግዚአብሄር ያለ ልክ ከፍ ከፍ አደረገዉ ከስምም ሁሉ በላይ ያለዉን ስም ሰጠዉ ይህም በሰማይና በምድር ከምድርም በታች ያሉትሁሉ በኢየሱስ ስም ይንበረከኩ ዘንድ መላስም ሁሉ ለእግዚአብሔር አብ ክብር ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እንደሆነ ይመሰክር ዘንድነዉ፡፡"*

ነገር ግን በዚህ በዮሴፍ ተምሳሌትነት ዉስጥ ሌላ ታላቅ መገለጥ ተመልከቱ በግብጽ ሳለ ከአህዛብ ሚስት ተሰጥቶትነበር ከእርሷም ሁለት ወንድ ልጆች ኤፍሬም እና ምናሴ የተባሉ አግኘ እናም ዮሴፍ አባቱን ሁለቱን ልጆች እንዲባርካቸዉ ጠየቀዉ ይባርካቸዉምዘንድ የበኩር ልጅ የሆነዉን

ምናሴን በያእቆብ ቀኝ ኤፍሬምን ደግሞ በግራዉ በኩል አስቀመጣቸዉ ያእቆብም ሊባርካቸዉ እጁን ባነሳጊዜ ቀኝ እጁ ታናሽየዉ ላይ ያርፍ ዘንድ ቀኝ ና ግራ እጁን አጠላለፈዉ፡፡ ዮሴፍም "አይደለም አባቴ ሆይ በቀኝህበኩል ያለዉ ነዉ የበኩር ልጅ" ብሎ ጮኸ ነገር ግን ያቆብ እንዲህ አለ እግዚአብሔር "እጆቼን አጠላለፋቸዉ" አለዉ በዚ ምሳሌ እምናየዉለበኩር ልጅ(ለአይሁድ) ይገባ የነበረዉ በረከት ለታናሹ ልጅ (ለአህዛብ) በእጅ መስቀል ሰርቶ በማጠላለፍ (መስቀል በሰራ እጅ)አማካኝነት በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስራ በመስቀሉ ስራ በኩል በረከት መጣ፡፡ ገላቲያ 3፥13-14

> *"በእንጨት የተሰቀለ ሁሉ የተረገመነዉ ተብሎ ተጽፎአልና ክርስቶስ ስለ እኛ እርግማን ሆኖ ከህግ እርግማን ዋጀን የመንፈስን ተስፋ በእምነት እንድንቀበል የአብርሃምበረከት ወደ አህዛብ በኢየሱስ ክርስቶስ ይደርሳቸዉ ዘንድ፡፡"*

የአብርሐም በረከት ወደ አህዛብ የመጣዉ በመስቀሉ በኩልነዉ፡፡ አይሁዶች መስቀሉን ተቃወሙ ስለዚህ ኢየሱስ የአህዛብን ሙሽሪት አገኛ፡፡

አሁን ደግሞ ዮሴፍወንድሞቹን ሲተዋወቃቸዉ ወዳለበት ታሪክ እንመለስ ካስታወሳችሁ ሁሉም ወንድሞቹ አልነበሩም የመጡት ዮሴፍም ይህን ያዉቅ ስለነበረሁሉም ወንድሞቹ እንዲገኙ ግድ አላቸዉ ካለበዚያ ግን ራሱን አይገልጥላቸዉም በስተመጨረሻም ትተዉት ቀርቶ የነበረዉን ታናሹንቢንያምን አመጡለት የዮሴፍ ሙሉ ወንድሞች ታናሹ ቢንያም ሲመጣ ነበር ነፍሱ እስኪቀጣጠል ያደረሰዉ እናም የእኛ ዮሴፍ የሆነዉኢየሱስ የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ወደ ጠበቁት ሰዎች እና ወደ ፍልስጤም ወደ ተመለሱት ሰዎች ይመጣና ነፍሱ እንደ እሳትትቀጣጠላለች፡፡ ትንሹ ቢንያም ለመቤዠት ሲሉ ከአለም ሁሉ ተሰብስበዉ ወደ ፍልስጤም የተመለሱትን እነዛ 144,000 እስራኤላዉያንንየሚያመላክት ነዉ፡፡ የዘላለም ህይወት የሆነዉን "እስከ ዛሬ የጠበቅነዉ አምላካችን" በማለት እሱን ለመቀበል ዝግጁ ይሆናሉ ከዛም የወጉትን እርሱንይመለከቱታል፡፡ "እነዚህ ቁስሎች ከየት መጡ? እንዴትስ ሊከሰት ቻለ?" በማለት ያዝናሉ ያለቅሳሉእያንዳንዱ ቤተሰብ እያንዳንዱ ሰዉ ያለቅሳል፡፡

ኢየሱስ እራሱን ለእይሁዶች በሚገልጥበት ጊዜ ታዲያ የአህዛብ ቤተክርስቲያን የት ነዉየምትሆነዉ? አስታዉሱ የዮሴፍ ሁለቱ ልጆች በቤተመንግስት ዉስጥ ነበሩ ምክንያቱም ዮሴፍ እንዲህ ብሎትእዛዝ አስተላልፎ ነበርና "ከፊቴ ሁሉም ሰዉ ይዉጣ በማት"የአህዛብ ሙሽሪት በዮሴፍ ቤተ መንግስት ዉስጥ ተሰዉራእንደነበረች የኢየሱስ ክርስቶስም የእህዛብ ሙሽሪት በንጥቀት ወደ ቤተ መንግስት ትወሰዳለች፡፡

ሙሽራይቱ ከምድር ትነጠቃለች ከታላቁ መከራ በፊት በአየርላይ ጌታዋን ለመቀበል ትነጠቃለች ለሶስት አመት ተኩል የእግዚአብሔር ቁጣ ሲወርድ እርሷ ግን በበጉ የእራት ግብዣ ስነስርአትላይ ትታደማለች ከዛም ሙሽራይቱን በአባቱ ቤት አስቀምጧት እራሱን ለወንድሞች ለማስተዋወቅ ይመለሳል በዚህ ጊዜ አይሁዶችከሀሰተኛዉ ክርስቶስ ከሮም ጋር ያደረጉት ኪዳን ይቋረጣል ሮም እና የጦር ሀይሎቿ እግዚአብሔርን የሚፈሩትን የቃል ኪዳንያላቸዉን አይሁዶች ለመዋጋት ጓዶቿን ትልካለች ነገር ግን ከተማይቱን ለማጥፋት ሲመጡ ያኔ የኢየሱስ መምጣት በሰማይ ምልክትይታያል ምድርን ያጠፏትን ሁሉ ለማጥፋት ከሰማይ ታላላቅ ጦሮችን ይዞ ያጠፋቸዋል ጠላቶቹንም ካጠፋ በኃላ ኢየሱስ እራሱን ለ144,000ዎቹ ይገልጥላቸዋልየማዳኑን ታላቅ ስራ በማየታቸዉም የእርሱን ሃያልነት ያዉቃሉ ነገር ግን ደግሞ የተወጉት እጆቹን እና ቁስሉንም ባዩት ቅጽበትምበመሸበር እና በፍርሃት ያለቅሳሉ ልክ የዮሴፍ ታላላቅ ወንድሞቹ በዮሴፍ ፊት ሲቆሙ የሚገድላቸዉ መስሏቸዉ በፍርሀት እንደቆሙሆኖም ግን ዮሴፍ "አይዟችሁ እራሳችሁን አትጉዱ እግዚአብሔር ህይወትን ያድን ዘንድ እርሱ ልኮኛልና በሁሉምነገር እግዚአብሔር ነበረበት" እንዳላቸዉ ኢየሱስም እንዲሁ ሰላምና ፍቅር ለእናንተ ይሁን ይላቸዋል፡፡

ለምንድን ነዉ አይሁዶች ኢየሱስን ያልተቀበሉት? በዛም ዉስጥ እግዚአብሔር ነበር የአህዛብን ሙሽሪትያገኝ ዘነድ ብቸኛ መንገዱ ያ ስለነበረ ነዉ፡፡ እርሱ በመስቀል ላይ የሞተዉ ከአህዛብ ቤተክርስቲያን ህይወትን ይታደግ ዘንድነዉ፡፡

እነዚህ 144000 ዎቹ ከሙሽራይቱ መካከል አይደሉምራእይ 14፡4 ላይ እንደተገለጸዉ ደናግሎች ናቸዉ በጉን ወደ ሄደበት ሁሉ ይከተሉታል ከሴት ጋር እራሳቸዉን ያላሳደፉበት እዉነታየሚያሳየዉ ጃንደረባዎች መሆናቸዉን ብቻ ነዉ (ማቴ 19፡12) ጃንደረባዎች ደግሞ የሙሽራይቱ አዳራሽ ጠባቂዎች ናቸዉ፡፡ተሳታፊዎች ናቸዉ፡፡ አስተዉሉ በዙፋኑ ላይ አብረዉ አልተቀመጡም ከዙፋኑ ፊት ናቸዉ እንጂ ከሙሽራይቱ መካከል አይደሉም ነገርግን በታላቁ የሚሊንየም ግዛት ይታደማሉ፡፡

እናም እስራኤል ከጌታ ጋር በፍቅር በምትቀላቀልበት ጊዜእና ጠላቶቿ ሲጠፉ እግዚአብሔር ቅድስቲቱን ተራራ ያዘጋጃታል አዲሲቱ የኤደን ገነት ለሙሽራይቱ እና ለ ታዳሚዎቹ የአንድ ሺህአመት የምድር ላይ የጫጉላ ሽርሽር ይሆናል አዳም እና ሔዋን በገነት ዉስጥ እንደነበሩ ነገር ግን የሺህ አመቱን ጉዞእንዳልጨረሱት ሳይሆን አሁን ግን ኢየሱስ የእኛ የመጨረሻ አዳም እና ሔዋን(እዉነተኛዋ ቤተክርስቲያን) የእግዚአብሔርን ሙሉእቅዱ ይፈጽማሉ፡፡

ኦ! እንዴት ባለ መልኩ መጽሃፍ ቅዱስ እራሱን ይደግማልየዮሴፍ እና የወንድሞቹ ትእይንት ኢየሱስ እየመጣ ስለሆነ ሊደገም ነዉ፡፡

ዬሴፍን ተምሳሌትነት እያበቃን በዚ ባለንበት የመጨረሻዘመን አንድ ነገር ትኩረት እንዳተደርጉ እፈልጋለሁ ወንድሙ ቢንይም ባልመጣበት ጊዜ ምንም እንኳን የእብራዊያን ቋንቋ ቢያዉቅምበአስተርጓሚ ነበር ይነጋገር የነበረዉ ለወንድሞቹ በሌላ ቋንቋ ነበር የሚያናግራቸዉ የመጀመሪያዉ የአህዛብ ቤተ ክርስቲያን(የወርቅ እራስ ያለዉ የባቢሎን ዘመን) በግድግዳ ላይ በተጻፉ ቋንቋዎች መልእክቱ እንደተሰራጨ ታዉቃልሁ በዚህ ዘመንም በተመሳሳይ መልኩ እየተስፋፋ ነዉ በዚህ ዘመንም ያለዉእጅግ ብዙ አይነት ቋንቋ የአህዛብ ሙላት እያበቃ መሆኑን ማረጋገጫ ነዉ እግዚአብሔር ወደ እስራኤል ፊቱን እያዞረነዉ፡፡

እርሱ እየመጣ ነዉ አልፋ እና ዖሜጋ ነብይ የሆነዉ ካህናችን የሆነዉ እና ንጉሳችን ሁሉበሁሉ የሆነዉ የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እየመጣ ነዉ፡፡ አዎ ጌታ ኢየሱስ ሆይ ያለህ እና ብቸኛ እዉነተኛ አምላክ ሆይ ቶሎና!

www.messagehub.info

ስብከት በ

## ዊልያም ማርዮን ብራንሀም

"... ድምጹም በሚሰማበት ዘመን ..." ራእይ 10፡7